# ጥናት 3 - ትምህርተ ፍጥረት

## የምዕራፎች ማውጫ


**ክፍል 1 - ምድራውያን ፍጡራን**

ምዕራፍ 29 - የእግዚአብሔር ዕቅድ . . . . . . . . . 261
ሀ) የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያብራሩ ቃላት . . . . . . . 261
ለ) የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁኔታ . . . . . . . . . 261
ሐ) የእግዚአብሔርን ዕቅድ የምንረዳባቸው የአመለካከት አቅጣጫዎች . 264
መ) የእግዚአብሔር ዕቅድ ትምህርት አቀራረብ . . . . . . . 264
ምዕራፍ 30 - ስለ ፍጥረት የእግዚአብሔር አስተርእዮ . . . . . 265
ሀ) የፍጥረት ታሪክ አገላለጥ . . . . . . . . . 265
ለ) የፍጥረት ታሪክ ዋና ነጥቦች . . . . . . . . 267
ሐ) የፍጥረት ታሪክ ትርጒም በመጽሐፍ ቅዱስ . . . . . . 271
መ) የቅድስት ሥላሴ ሥራ በፍጥረት . . . . . . . . 272
ምዕራፍ 31 - ስለ ፍጥረት የእግዚአብሔር አስተርእዮ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ 274
ሀ) የዓለም ህልውና . . . . . . . . . . . 274
ለ) የዓለም ዕድሜ . . . . . . . . . . . 275
ሐ) የሰው ዕድሜ . . . . . . . . . . . . 276
መ) የሰው አመጣጥ . . . . . . . . . . . 278
ሠ) በፍጥረቱ የእግዚአብሔር ዓላማ . . . . . . . 281
ምዕራፍ 32 - የፍጥረት አጠባበቅ . . . . . . . . . 283
ሀ) በፍጥረት ላይ ሊኖር የሚገባው አመለካከት . . . . . . 283
ለ) የፍጥረት አጠቃቀም . . . . . . . . . . 284
ሐ) የፍጥረት ተስፋ . . . . . . . . . . . 286

**ክፍል 2 - ሰማያውያን ፍጡራን**

ምዕራፍ 33 - መላእክት . . . . . . . . . . . 288
ሀ) አፈጣጠራቸውና ሁኔታቸው . . . . . . . . . 288
ለ) ልዩ ልዩ መጠሪያዎቻቸውና ስሞቻቸው . . . . . . . 289
ሐ) ሌሎች ሰማያውያን ፍጡራን . . . . . . . . 290
መ) አገልግሎታቸው . . . . . . . . . . . 291
ሠ) ከምእመናን ጋር ያላቸው ግንኙነት . . . . . . . 292
ረ) ለመላእክት አገልግሎት የምእመናን አጸፋ . . . . . . 293
ምዕራፍ 34 - ሰይጣንና መላእክቱ . . . . . . . . 296
ሀ) የሰይጣንና የክፉ መላእክት ውድቀት . . . . . . . 296
ለ) የሰይጣን ሥልጣን . . . . . . . . . . . 297
ሐ) የሰይጣንና የመላእክቱ ሥራና አሠራር . . . . . . . 298
መ) ሰይጣንንና መላእክቱን ድል ለማድረግ የምእመናን ሥልጣን . . . 301

## ክፍል 3 - የፍጥረት አስተዳደር

ምዕራፍ 35 - መግቦተ እግዚአብሔር . . . . . . . . . . 306
ሀ) እግዚአብሔር ሁሉን ይሰብቃል . . . . . . . . . 307
ለ) እግዚአብሔር ሁሉን ያንቀሳቅሳል . . . . . . . . 307
ሐ) እግዚአብሔር ሁሉን ይቈጣጠራል . . . . . . . . 309
መ) እግዚአብሔር ተአምራትን ያደርጋል . . . . . . . 310
ምዕራፍ 36 - ትምህርተ መግቦተ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ . . 319
ሀ) በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አጠቃቀም . . . . . . . 322
ለ) እግዚአብሔር ክፋትን እንዴት እንደሚጠቀምበት . . . . . 323
ሐ) የነጻነት ትርጒም . . . . . . . . . . . . 326
መ) የመግቦተ እግዚአብሔር ትምህርት ውጤት . . . . . . 327
ምዕራፍ 37 - ፍትሐ እግዚአብሔርና ክፋት . . . . . . . 330
ሀ) ስለ ክፋት ልዩ ልዩ አመለካከቶች . . . . . . . . 331
ለ) ስለ ክፋት የመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ . . . . . . . 333
ሐ) ስለ ክፋት የእግዚአብሔር አሠራር . . . . . . . . 334
መ) ስለ ክፋት የድል መንገድ . . . . . . . . . . 336

# ጥናት 3 - ትምህርተ ፍጥረት

## ክፍል 1 - ምድራውያን ፍጡራን

## ምዕራፍ 29 - የእግዚአብሔር ዕቅድ

«እግዚአብሔር ሆይ፥ ሥራህ እንዴት ብዙ ነው! ሁሉን በጥበብ ሠራህ፤ ምድርም በፍጥረትህ ተሞላች»፤ መዝ. 104፥24 አ.መ.ት.

በትምህርተ አስተርእዮ እግዚአብሔር ራሱን እንዴት እንደገለጠና በትምህርተ ባሕርየ እግዚአብሔር እንዴት ያለ አምላክ መሆኑን ካላየን በኋላ ሥራውን መመርመር አመክንዮታዊ ነው። ከሰው ሥራ ሁሉ የእግዚአብሔር ሥራ የተለየ ነው፤ ምክንያቱም በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ሲፈጥር ከሚታየው ነገር አልሠራም። ስለ እግዚአብሔር አሠራር በአጠቃላይ ስናስብ፥ «ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው ...» የሚለው ሐረግ ዐቢይ አሳብ ሊሆንልን ይችላል፤ ኤፌ. 1፥11 አ.መ.ት.። ይህ ቃል ከእግዚአብሔር ባሕርይ መገለጫዎች ጋር፥ በተለይም ከሁሉን ቻይነቱ፥ ከልዕልናው፥ ከጥበቡና ከፈቃዱ ጋር ይስማማል። በዚህ ጥናት ስለ ፍጥረት ስናስብ፥ በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሥራውን ሁሉ እንዴት እንዳቀደ፥ በኋላም ዕቅዱ በፍጥረት ሥራው እንዴት እንደተፈጸመ መመርመር ይገባናል።

### ሀ) የእግዚአብሔርን ዕቅድ የሚያብራሩ ቃላት

የእግዚአብሔርን ዕቅድ በሙሉ ወይም በከፊል የሚያብራሩ ልዩ ልዩ ቃላት በቅዱሳት መጻሕፍት አሉ፤ እነርሱም በብሉይ ኪዳን፥ ምክር (ኢዮብ 38፥2፤ ኢሳ. 46፥10፤ ኤር. 23፥18:22)፥ አሳብና አሰበ (ኢሳ. 14፥26፤ ኤር. 4፥28፤ 51፥12)፥ ፈቃድ (ኢሳ. 46፥10፤ 53፥10) እና ዐወቀ (ሆሴዕ 13፥5፤ አሞጽ 3፥2) ሲሆኑ፥ በአዲስ ኪዳን ደግሞ ምክር (ኤፌ. 1፥11)፥ አሳብ (ሐ.ሥ. 2፥23፤ ኤፌ. 1፥11፤ 2ጢሞ. 1፥9)፥ ዕውቀትና ዐወቀ (ሐ.ሥ. 2፥23፤ 2ጢሞ. 2፥19፤ 1ጴጥ. 1፥1-2)፥ ምርጫና መረጠ (ሮም 8፥33፤ 9፥11፤ ኤፌ. 1፥4፤ 2ተሰ.-2፥13)፥ ፈቃድ (ማቴ. 11፥26፤ ኤፌ. 1፥5:9፤ ዕብ. 6፥17-18) እና ወሰነ (ሐ.ሥ. 4፥27-28፤ ሮም 8፥29፤ ኤፌ. 1፥5:11) የሚሉት ናቸው።

### ለ) የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁኔታ

የእግዚአብሔርን ዕቅድ ሁኔታ በስድስት አርእስት አጠቃልለን ለመመልከት እንሞክራለን።

1. የእግዚአብሔር ዕቅድ ነጻ ነው

በእግዚአብሔር ዘንድ ባሕርያዊ ፈቃድና ኢባሕርያዊ ፈቃድ እንዳሉ አስቀድመን አይተናል (ም. 24 ሸ1)። ፍጥረትን በተመለከተ እግዚአብሔር ዓለምን የመፍጠር ግዴታ አልነበረበትም፤ እርሱ በነጻ ፈቃዱ ዓለምን ፈጥሮታልና። ቢፈልግም ኖሮ ዓለምን በሌላ ዐይነት ሊፈጥር እንደሚችል ማሰብ አይከብድም። ሲፈጥረው እንደ ባሕርዩ እንጂ ባሕርዩን የሚፃረር አልነበረም። እንደ ቸርነቱ ሁሉን መልካም አድርጎ ፈጠረ።

2. የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ ነው

የእግዚአብሔር ሥራ ብዙ ቢሆንም ዕቅዱ አንድ ነው። እግዚአብሔር «እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን ይሠራል»፤ ሁሉንም ስለሚያውቅና በጊዜ ስለማይወሰን ሁሉን በአሳቡ በአንድነት ማየትና መወሰን ሲችል፥ ሁሉንም በአንድ ዓላማ ወደ አንድ ግብ እንዲራመድ በሁሉን ቻይነቱ ያደርጋል። ስለዚህ በዓለም የሚሆነው ሁሉ በእግዚአብሔር አስቀድሞ ተወስኖ ነበር። ሰው እጅግ ውሱን በመሆኑ፥ ይህን መረዳትና ማስተዋል አይችልም፤ ክርስቲያን ግን በእግዚአብሔር አምኖና ተስፋ አድርጎ ሁሉን ከእጁ ሲቀበል ወደ ፍቅሩ፥ ወደ ደግነቱና ወደ ዕቅዱ እየተመለከተ ፍጻሜውን በትዕግሥት ይጠብቃል።

3. የእግዚአብሔር ዕቅድ ጥበብ አለበት

ዳዊት፥ «ሁሉን በጥበብ አደረግህ» ብሎ ዘመረ፤ መዝ. 104፥24። ሰሎሞን፥ «እግዚአብሔር በጥበብ ምድርን መሠረተ» ብሏል፤ ምሳ. 3፥19፤ ኤር. 10፥12፤ 51፥15። የእግዚአብሔር ምክር በመጽናቱ ጥበቡ ይታያል፤ መዝ. 33፥11፤ ምሳ. 19፥21። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው የዘለዓለም አሳብ ነበረ» በማለት የእግዚአብሔር ጥበብ በፍጥረት ብቻ ሳይሆን በሰው መዳንና በቤተ ክርስቲያን መገለጡን ያሳያል፤ ኤፌ. 3፥10-11።

4. የእግዚአብሔር ዕቅድ ዘለዓለማዊ ነው

ዓለም ሳይፈጠር ፍጥረት እንደታቀደ ግልጥ ነው። ሆኖም በዓለም ታሪክ ውስጥ የሚሆነው ሁሉ የእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ አሳብ ነው፤ ኤፌ. 3፥10-11። ሰው በኀጢአት ቢወድቅምና በሥራው ብቃት ባይኖረውም፥ ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ ተመረጠ፤ ኤፌ. 1፥4፤ 2ጢሞ. 1፥9።

ዕቅዱ በሙሉ ወይም በከፊል በጊዜ ውስጥ አይወሰንም፤ ከዓለምና ከጊዜ በፊት ተወስኗልና፤ ዕቅዱ ዘለዓለማዊ ነው። ዕቅዱ ዘለዓለማዊ ቢሆንም፥ እንደ ፍጥረት፥ እንደ ሰው ደኅንነት እና እንደ መጨረሻው ፍርድ ያሉት የዕቅዱ ክፍሎች በዓለም ታሪክና ጊዜ ውስጥ ይደረጋሉ፤ ይታያሉ፤ ይፈጸማሉም።

5. የእግዚአብሔር ዕቅድ አይቀሬ ነው

እግዚአብሔር ያቀደው እንደ አሳቡና እንደ ምክሩ ይፈጸማል። በሚከተለው ምዕራፍ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ በቃሉ ቀጥታ ይፈጥራል፤ ሌላ ጊዜም በቃሉ ከፈጠረው ነገር ሌላውን ነገር ያደርጋል፤ ለምሳሌ «ሰውን ከምድር ዐፈር አበጀው»፤ ዘፍ. 2፥7።

በሰው ዘንድ የእግዚአብሔር ዓላማ እንዲፈጸም በዕቅዱ ውስጥ አስፈላጊ መሣሪያዎቹ ይገኛሉ። ለምሳሌ ክርስቶስ እንዲሞት ክፉ ሰዎች ለዐመፅ ዝግጁዎች ሆነው መገኘታቸው (ሐ.ሥ. 2፥23)፥ አስቀድሞ የተዘጋጀውን መልካሙን ሥራ እንዲያደርግ ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ መፈጠሩ (ኤፌ. 2፥8-10) እና ቆርኔሌዎስ እንዲድን ሐዋርያው ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ መዘጋጀቱ (ሐ.ሥ. 10፥17-23፤ 11፥18) በዕቅዱ ተመድቦ ነበር።

እግዚአብሔር በሰው አማካይነት ሲሠራ፥ የሚጠቀምበት ሰው ነጻነት እንዲኖረው፥ ሁኔታውና ዐውዱ ሳይለወጥ እንዲቀጥል፥ ሰውዬው እንደ ጠባዩና እንደ ፈቃዱ

የሚያደርገውን እንዲያደርግ፥ ዕቅዱ ይወስናል፤ ምሳ. 19፥21፤ ኢሳ. 46፥10። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር ዕቅዱን እንዲለውጥ አያስፈልግም፤ አይለውጠውምም።

6. የእግዚአብሔር ዕቅድ ሁሉን ያጠቃልላል

በተፈጥሮአዊና በግብረገባዊ ዓለማት ሳይቀር ከዕቅዱ ውጭ አንድም ነገር፥ እንስሳ፥ ሰው፥ መልአክም እንኳ የለም፤ ኤፌ. 1፥11። ዕቅዱ የሰውን መልካም ሥራ (ኤፌ. 2፥10) እና ክፉ ሥራ (ምሳ. 16፥4፤ ሐ.ሥ. 2፥23፤ 4፥27-28)፥ ከሰው ድርጊት የተነሣ የሚገኘውን ውጤት (ዘፍ. 45፥8፤ 50፥20፤ ምሳ. 16፥33)፥ ፍጻሜንና ወደ ፍጻሜ ማድረሻውን (መዝ. 119፥89-91፤ ኤፌ. 1፥4፤ 2ተሰ. 2፥13)፥ የሰውን ዕድሜ (ኢዮብ 14፥5፤ መዝ. 39፥4) እና መኖርያውን (ሐ.ሥ. 17፥26-27) ያጠቃልላል።

የእግዚአብሔር ዕቅድ ክፋትን እንዳይፈጸም አያደርገውም፤ በዚህም እግዚአብሔር የክፋት ፈጻሚውን ነጻነት፥ ፈቃድ፥ ኀላፊነትና ተጠያቂነት ይጠብቃል፤ የክፋትን ውጤትም ይወስናል፤ መዝ. 78፥29፤ 106፥15፤ ሐ.ሥ. 14፥16፤ 17፥30፤ ሮም 11፥32።

ከዚህ በላይ የተጻፈው ትምህርት ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ ሦስት ዐይነት ጥያቄዎችን ያስነሣልና በዐጭሩ ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እንሞክራለን።

ሀ) ትምህርቱ የሰውን ግብረገባዊ ነጻነት አያሳጣምን? የሚሆነውን ሁሉ እርሱ ስለሚወስን ለሰው ምን ዐይነት ነጻነት ቀርቷል? ለዚህ ጥያቄ የምንሰጠው መልስ እንደሚከተለው ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ የእግዚአብሔር ዕቅድ በነጻነት የሚሠራውን የሰው ድርጊት አስቀድሞ ሲወስን፥ ለሚሠራው ሁሉ ኀላፊ መሆኑን ያሳያል። በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሓፊዎች ዘንድ ለምሳሌ ስለ ዮሴፍና ወንድሞቹ ወይም ስለ ክርስቶስ ስቅለት ሲጽፉ፥ በሁለቱ አሳቦች መካከል ግጭት ወይም አለመግባባት ያለ ስለ መሆኑ ምንም ፍንጭ አይታይም፤ ዘፍ. 50፥19-20፤ ሐ.ሥ. 2፥23፤ 4፥27-28። ይህ ለእኛ ምሥጢር ነው፤ ሆኖም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንደ ተፈጥሮአቸውና እንደ ጠባያቸው የሰዎች ነጻ ድርጊቶች በዕቅዱ ውስጥ ደግሞ ይገኛሉ።

ለ) ትምህርቱ፥ ዕቅዱ አይቀሬ በመሆኑ ሰው መልካም ሥራን ለመሥራት የሚያደርገውን ጥረት አያስቀርምን? ይህ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ከስንፍና የተነሣ የሚቀርብ ጥያቄ ነው። እግዚአብሔር ግን ሰው የሚዘራውን እንደሚያጭድ የወሰነ በመሆኑ (ገላ. 6፥7)፥ ዕቅዱ መልካም እንዲሠራ ሰውን ይቀሰቅሰዋል፤ ፊል. 2፥12-13።

ሐ) ትምህርቱ እግዚአብሔርን የኀጢአት ምንጭ አያደርገውምን? ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ የዕቅዱን ትምህርታዊነት ያስቀር ነበር፤ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ፥ እግዚአብሔር ቅዱስና ብርሃን መሆኑን፥ ሰውንም በክፉ እንደማይፈትን ያስተምራል፤ 1ዮሐ. 1፥5፤ ያዕ. 1፥13። እግዚአብሔር ግን የነጻ ግብረገባዊ ሰዎች ፈጣሪ ነው፤ እነርሱም የክፋት ምንጮች ናቸው። እግዚአብሔር በዕቅዱ ነጻነታቸውን ይጠብቃል፤ የሕይወታቸውንም ዐውድ ይወስናል። በዕቅዱ መልካምም ሆነ ክፉ ሥራቸው አይቀሬ ነው፤ ሰው ክፉ ምኞት እንዲኖረውና ክፉ ሥራ እንዲመርጥ ግን አያደርገውም፤ አያስገድደውምም። የእግዚአብሔር ዕቅድ ከሰው ነጻነት ጋር እንዴት እንደሚገናኝ «መግቦተ እግዚአብሔር» እና «ፍትሐ እግዚአብሔርና ክፋት» በሚሉት ምዕራፎች በሰፊው ለመመርመር እንሞክራለን።

## ሐ) የእግዚአብሔርን ዕቅድ የምንረዳባቸው የአመለካከት አቅጣጫዎች

የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ ቢሆንም እርስ በርስ በተያያዙ ሦስት መንገዶች ልንመለከተው እንችላለን።

1. እግዚአብሔርን በተመለከተ ዕቅዱ የራሱን ክብር እንዴት እንደሚገልጥ ያሳያል። በዚህ አመለካከት «ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም» በመሆኑ ለእርሱ ለዘለዓለም ክብር መስጠት እንደሚገባን እናያለን፤ ሮም 11፥36። ይህ መጽሐፍ በተለይ ይህን አመለካከት ያብራራል።

2. ኀጢአተኛን በተመለከተ ዕቅዱ ወልድ ሰው ሆኖ ኀጢአተኛውን እንዴት እንዳዳነ ያሳያል። በዚህ አመለካከት ኢየሱስ ሕዝቡን ከኀጢአታቸው እንደሚያድን እናያለን፤ ማቴ. 1፥21። 2ኛው መጽሐፋችን «ትምህርተ ክርስቶስ» በዚህ አመለካከት ላይ ያተኵራል።

3. ታሪክን በተመለከተ ዕቅዱ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በመቀጠል የእግዚአብሔር መንግሥት በሰው ፍጥረት፥ ውድቀት፥ መታደስና መከበር ሁኔታዎች ውስጥ ሥር እየሰደደ ሲሄድ ወደ ፍጻሜ እንዴት እንደሚደርስ ይገልጣል። በዚህ አመለካከት ክርስቶስ ለበጎቹ የተዘጋጀላቸውን መንግሥት እንዴት እንደሚያወርስ ያሳያል፤ ማቴ. 25፥34። 3ኛው መጽሐፋችን «ትምህርተ መንፈስ ቅዱስ» በተለይ ይህን አመለካከት ያብራራል።

የእግዚአብሔር ዕቅድ አንድ ነው። ሆኖም ሰው በሦስት አመለካከት ወይም በሦስት መንገዶች ቢመረምረው ሊረዳው ይችላል። በዕቅዱ ውስጥ ሦስት ታላቅ ምግባሮች ይታያሉ፤ እነርሱም ፍጥረት፥ ደኅንነትና ሥነ ፍጻሜ ናቸው። የሥላሴ አካላት ምንም እንኳ በአንድነት በምግባር ሁሉ ቢሳተፉም፥ አብ በፍጥረት፥ ወልድ በደኅንነት፥ መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በሥነ ፍጻሜ በጕልሕ ይሠራሉ።

## መ) የእግዚአብሔር ዕቅድ ትምህርት አቀራረብ

BERKHOF፥ ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ ያለውን ትምህርት ትምህርተ ሥላሴና ትምህርተ ፍጥረት በተሰኙት ሁለት ምዕራፎች መካከል አስቀምጦታል። GRUDEM ግን በትምህርተ ሥላሴና በትምህርተ ፍጥረት መካከል ምንም አልጻፈምና ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ ያለውን ትምህርት በልዩ ልዩ ቦታ ገልጦታል።

እኛም በዚህ ምዕራፍ ስለ እግዚአብሔር ዕቅድ አጠቃላይ ትምህርት ለመስጠት ሞክረናል፤ ሆኖም ፍጥረትን፥ ደኅንነትንና ሥነ ፍጻሜን የተመለከተውን የእግዚአብሔር ዕቅድ ትምህርት ለየብቻው ከምግባር ትምህርት ጋር ለመስጠት አስበናል፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ አቀራረብ ነው።

እንግዲህ ሀ) በዚህ ጥናት እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት እንደፈጠረና እንዴት እንደሚያስተዳድረው ስንገልጥ የዕቅዱ ዓላማ ምን እንደሚመስል፥

ለ) በሁለተኛው መጽሐፍ ክርስቶስ ሰውን እንዳዳነና በተለይ በዚህ ምግባር ውስጥ ዕቅዱ እንዴት እንደተፈጸመ፥

ሐ) በሦስተኛው መጽሐፍ መንፈስ ቅዱስ ሰዎችን ወደ ደኅንነት፥ ወደ ቤተ ክርስቲያን አባልነትም እንዴት እንደሚያደርሳቸውና በዘለዓለም በረከት እንዴት እንደሚጠብቃቸው፥ እንደዚሁም ክርስቶስ በዳኑትና ባልዳኑት ላይ ሲፈርድ ዕቅዱ ምን እንደሆነ እናትታለን።

# ምዕራፍ 30 - ስለ ፍጥረት የእግዚአብሔር አስተርእዮ

ብሉይ ኪዳን ለአዲስ ኪዳን፥ ፔንታቱክ (አምስቱ የኦሪት መጻሕፍት) ለብሉይ ኪዳን፥ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1-11 ለፔንታቱክ፥ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1 ደግሞ ለምዕራፍ 1-11 መግቢያ ናቸው። እንግዲህ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን በሚገባ ካልተረዳን የመጽሐፍ ቅዱስ አተረጓጐማችን በሙሉ የተዛባ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ምዕራፍ ሊቃውንት ብዙ አሳብ ይኖራቸዋልና እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ ምን እንደሚያስተምረን በጥንቃቄ መመልከት አለብን።

## ሀ) የፍጥረት ታሪክ አገላለጥ

ዓለም ሲፈጠር ሰው አልነበረምና እግዚአብሔር ካልገለጠለት በስተቀር ሰው ስለ ዓለም አፈጣጠር ሊያውቅ አይችልም ነበር። እግዚአብሔር መጀመሪያ ይህን ለማን ወይም እንዴት እንደገለጠው አናውቅም፤ ታሪኩ መጀመሪያ የሚገኘው በኦሪት ዘፍጥረት ነው፤ ሙሴም የኦሪት ጸሐፊ መሆኑ ይታመናል (1)። እንግዲህ የመጀመሪያ አንባቢዎችና ሲነበብ የሚሰሙቱ ከግብጽ ወጥተው በምድረ በዳ የነበሩት የእስራኤል ሕዝብ መሆናቸውን ማሰብና መረዳት ይቻላል። ስለ ምዕራፉ አጠቃላይ ሁኔታ ስናስብ የሚከተሉት ነጥቦች ሊረዱን ይችላሉ።

1. «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ» የሚለው ዐረፍተ ነገር የሚቀጥለውን ያሳስባልና እንደ ምዕራፍ ርእስ ሊቈጠር ይችላል፤ ዘፍ. 1፥1። የተፈጠረው ሁሉ በሁለት ተከፍሎ ይታያል። ምድር ሲል ሰው የሚኖርበትን ዓለም ያመለክታል። ሰማያት ሲል ደግሞ ከምድር በላይ ያለውን ሁሉ ያሳያል። በዕብራይስጥ ቋንቋ ቃሉ በብዙ ቍጥር የተጻፈ ሲሆን፥ በግሪክ ግን ነጠላም ሊሆን ይችላል፤ ለምሳሌ ማቴ. 24፥35፤ ሉቃ. 15፥18፤ ዮሐ. 3፥27፤ ራእ. 21፥1-3። እንደ ዐውዱ ሰማያት ወይም ሰማይ ቍሳዊ ሁኔታን ሊያመለክት ይችላል፤ እግዚአብሔር ጠፈርን ሰማይ ብሎ ጠርቶታልና፤ ዘፍ. 1፥8። አንዳንዶች፥ የድሮ ሰዎች ጠፈርን እንደተዘቀዘቀ ጕድጓዳ ሳሕን ይመለከቱት የነበረ ይመስላቸዋል። ፀሓይዋ በየቀኑ በሰማያት ላይ ትመላለስባቸዋለች (መዝ. 19፥5-6)፤ ዝናብ በሰማይ መስኮቶች ዐልፎ በምድር ላይ ይወርዳል፤ ዘፍ. 7፥11። ከጥንት ሰዎች የተወሰኑት ይህን በቁሙ ቢመለከቱትም፥ የዕብራይስጥ ጸሓፊዎች በብዙ ምሳሌ እንደተጠቀሙ እናውቃለንና በዚህ አመለካከት የተወሰኑ አይመስልም። ሰማያት የእግዚአብሔርን መኖሪያና ኢቍሳዊውን ሁኔታ ሲያመለክቱ፥ ከእርሱ ጋር ያሉ ሠራዊት (ዘፍ. 2፥1)፥ መላእክት (ማር. 13፥2) እና በእርሱ አምነው ያረፉ ነፍሳት አብረው ይገኛሉ፤ ሉቃ. 23፥43፤ ዕብ. 12፥22:23። የአሁኖቹ ሰማያት የተፈጠሩ በመሆናቸው ጊዜያውያን ናቸውና በዓለም መጨረሻ አዲስ ሰማይና አዲስ ፍጥረት ይገኛል፤ 2ጴጥ. 3፥10-13፤ ራእ. 21፥1-3። አንዳንዶች በተለይ አይሁድ ሰማያት የብዛት ቃል በመሆኑ እስከ ሰባት ደረጃዎች በሰማይ እንዳሉ አስበዋል። እውነት ነው፤ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገነት፥ ስለ ሦስተኛው ሰማይ (ሉቃ. 23፥43፤ 2ቆሮ. 12፥2)፥ እንደዚሁም ክርስቶስ በሰማያት እንዳለፈ ይናገራል፤ ዕብ. 4፥14። ሆኖም እነዚህ ጥቅሶች ለዚህ ትምህርት በቂ መሠረት የሚሆኑ አይመስሉም። ሰማይ ወይም ሰማያት ፍጹምነት ያለበትን ስፍራና ሁኔታ የሚያመለክቱ እንደሆነ ማሰብ ይሻላል፤ «ሰማይ» በመቅመቃ. ይመ.።

አንዳንድ ሰዎች በቍጥር አንድና በቍጥር ሁለት መካከል ረጅም ዘመን እንደነበረ ያስባሉ (2)። በዚህ አስተሳሰብ መሠረት ቍጥር 2 ምድር «ባዶ» በመሆኑና «ጨለማ» በጥልቁ ላይ በመገኘቱ እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ዐመፀና ፍጥረቱን እንዳፈረሰ (ወይም እግዚአብሔር እንደፈረደበት) ያሳያል። እንደዚህ ከሆነ የምዕራፉ ስድስት ቀኖች የፍጥረት ሥራ የማሳደስ ሥራ እንጂ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ሥራ አልነበረም። ይህን አስተሳሰብ በልዩ ልዩ ምክንያት መቀበል ግን የተሻለ አማራጭ አይመስልም (3) :-

ሀ) ከዚህ በታች እንደምንመለከተው ከጠቅላላው ምዕራፍ አገላለጥ ጋር አይስማማም።

ለ) በመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ጥቅስ ስለ «ፊተኛው» ፍጥረት አይናገርም።

ሐ) በስድስተኛው ቀን እግዚአብሔር ያጠናቀቀውን ሥራ ሲያይ «እጅግ መልካም ነበረ»፤ ዘፍ. 1፥31። የፊተኛው ረጅም ዘመን መላምት ትክክለኛ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ፍርድ የወደቀበትን ዓለም ይመለከት ነበር።

መ) «ሰማያትና ምድር ሠራዊታቸውም ሁሉ ተፈጸሙ» (2፥1) የሚለውን የምዕራፍ አንድ መደምደሚያ ስንመለከት፥ ይህ መላምት ትክክለኛ ከሆነ፥ ሰይጣንና ተከታዮቹ በፍጥረቱ መካከል ነበሩበት ለማለት ያስደፍራል። እነርሱን ግን «እጅግ መልካም» ማለት አይቻልም፤ 1፥31።

ሠ) «እግዚአብሔር በስድስት ቀን ሰማያትንና ምድርን፥ ባሕርንም፥ ያለባቸውንም ሁሉ ፈጥሮ ...» የሚለው ሁሉ በስድስት ቀኖች እንጂ ከስድስቱ ቀኖች በፊት ምንም እንዳልተፈጠረ ያሳያል፤ ዘጸ. 20፥11።

ስለዚህ በቍጥር አንድና በቍጥር ሁለት መካከል ጸሐፊው ረጅም ዘመን እንደነበረ የሚያስብ አይመስልምና «መጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ፈጠረ» የሚለውን ለምዕራፉ እንደ ርእስ አድርጎ መመልከት ተገቢ ይመስላል።

2. ከጸሐፊው ግቦች አንዱ ሰው የእግዚአብሔርን ፍጥረት ሥራ ተረድቶ ስድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ቀን እንዲያርፍ ነበረ፤ ዘፍ. 2፥1-3፤ ዘጸ. 20፥11። በዚህ ምክንያት በሰው የአሠራር ምሳሌነት የፍጥረቱን ታሪክ ያቀርባል። ለምሳሌ ሰው አንድ ቤት ለመሥራት ሲፈልግ አስፈላጊውን ዕቃ ሁሉ ከሰበሰበ በኋላ እንደ ዕቅዱ በቅደም ተከተል ሥራውን ማከናወን ይቀጥላል፤ በየቀኑም የሠራውን ይመለከታል። ሥራውንም ከጨረሰ በኋላ ዐርፎ ይደሰትበታል። በዚህ አስተሳሰብ እግዚአብሔር ቍስ አካል ያለውን ነገር ሁሉ መጀመሪያ ከማይታየው ወይም ከምንም ሲፈጥር «ባዶ» ነበረ። አንዳንዶች ቍ. 1 ከአለመኖር ወደ መኖር የፍጥረትን ሥራ እንደማያመለክት ያስባሉ፤ ከዚያም በኋላ በየቀኑ በተፈጠረው «ዕቃ» ተጠቅሞ እንደ ዕቅዱ ሠራ። ጸሐፊው፥ «ማታም ሆነ፤ ጧትም ሆነ ...» በማለቱ የእግዚአብሔርን አሠራር በሰው አሠራር ምሳሌ አድርጎ የሚገልጥ ይመስላል፤ ቍ.5:8:13:19:23:31።

3. «እግዚአብሔር ሁለት ታላላቅ ብርሃናትን አደረገ፤ ትልቁ ብርሃን በቀን እንዲሠለጥን፥ ትንሹም ብርሃን በሌሊት እንዲሠለጥን ... አደረገ» በፀሐይ ፈንታ «ትልቅ ብርሃን» እና በጨረቃ ፈንታ «ትንሽ ብርሃን» ብሎ በመጻፉ፥ የእግዚአብሔር ሕዝብ በዙሪያቸው እንደሚገኙ አሕዛብ እንዳያደርጉ ፀሐይንም ሆነ ጨረቃን እንዳያመልኩ ያሳሰባቸው ይመስላል፤ እነርሱ ፈጣሪያቸውን ብቻ ማምለክ ነበረባቸውና፤ ቍ. 16።

4. በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድና ሁለት መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት ማተት አስፈላጊ ነው። ምዕራፍ አንድ ስለ ሰው ፍጥረት ቢናገርም፥ በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ ያተኩራል፤ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ይላልና። ምዕራፍ 2፥1-3 በሁለቱ ምዕራፎች መካከል እንደ ድልድይ የሚታይ ክፍል ነው። ምዕራፍ 2 ደግሞ በእግዚአብሔር ፍጥረት ውስጥ ሰው ባለው ስፍራ ላይ ያተኩራል። በዚህም ምክንያት በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር «እግዚአብሔር አምላክ» (ያህዌ ኤሎሂም) ተብሎ ይጠራል፤ ያህዌም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለውን ቃል ኪዳን የሚያመለክት ስም በመሆኑ፥ ጸሓፊው በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ሰው ባለው ስፍራ ላይ አተኰረ። ምዕራፍ ሁለትን «ትምህርተ ሰብእ» በሚለው በ4ኛው ጥናት በስፋት እንደምንመለከተው ተስፋ እናደርጋለን።

## ለ) የፍጥረት ታሪክ ዋና ነጥቦች

የፍጥረት ታሪክ በአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ሲገልጥ፥ ስለ ባሕርዩ ብዙ ነገሮችን ያሳያል። ዋና ዋና ነጥቦችን በሰባት ክፍሎች ለማብራራት እንሞክራለን።

1. እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሁሉን ፈጠረ፤ ዘፍ. 1፥1፤ 2፥1-2፤ ዘጸ. 20፥11። እንግዲህ ሀ) እግዚአብሔር ከፍጥረት በፊት ነበረ፥ ለ) ከፍጥረት በፊት ወይም ያለ ፍጥረት በራሱ ፍጹም ሆኖ እየኖረ ፍጡራንን በግዴታ ሳይሆን በፈቃዱ ፈጠረ፥ ሐ) ፍጥረት ከፈጣሪው የተለየ ነው፥ መ) ፍጥረት እግዚአብሔር አይደለም (4)፥ ሠ) ፍጥረቱ በእግዚአብሔር የተደገፈ እንጂ ከእግዚአብሔር ተለይቶ ያለ አይደለም፥ ረ) እግዚአብሔርና ፍጥረቱ ከዘለዓለም አብረው አልኖሩም (5)፥ ሰ) ጊዜና ስፍራ ከፍጥረት ጋር አብረው ተፈጠሩ፥ ሸ) እግዚአብሔር ያለውንና የሚታየውን ሁሉ ከምንም ወይም ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ፥ ቀ) ከሚታየው ፍጥረት ሌላ የማይታይ ፍጥረት አለ (6) ማለት እንችላለን።

2. እግዚአብሔር ሁሉን በቃሉ ፈጠረ፤ እግዚአብሔር ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃንም ሆነ፤ ዘፍ. 1፥3። እግዚአብሔር ሲፈጥር ረዳት፥ ጓደኛ ወይም ደጋፊ አላስፈለገውም ነበር። እግዚአብሔርም ቊስ አካልን ሁሉ ከፈጠረ በኋላ (ቊ.2) በስድስት ቀኖች አደራጀው። ይህንም ሲያደርግ ስምንት ጊዜ አዘዘ፤ እንዳዘዘም ተፈጸመ፤ ቊ. 3:6:9:11:14:20:24:26። እግዚአብሔር ሲናገር ፈቃዱን ይገልጣል፤ በሁሉን ቻይነቱ ፈቃዱ ይፈጸማል። ፈቃዱንም የሚፈጽመው በውሃዎች ላይ የረበበው መንፈሱ ነበረ፤ ቊ.2።

እግዚአብሔር ብርሃንን ሲፈጥር ከተፈጠረው ቊሳዊ ነገር ያመጣው ይመስላል፤ የፀሓይና የከዋክብት ብርሃን ከሃይድሮጅን ይገኛልና። ይህ ግልጥ ባይሆንም፥ እግዚአብሔር «ታብቅል» (ቊ.11)፥ «ታስገኝ» (ቊ.20) እና «ታውጣ» (ቊ.24) በማለቱ አስቀድሞ ከተሠሩት ነገሮች አዲስ ፍጥረቶችን አወጣ። ሰውንም ሲፈጥር ያደረገው እንደዚሁ ነው፤ 1፥27፤ 2፥7።

እንግዲህ ሁለት ዐይነት አፈጣጠር ነበረ፤ ይኸውም አንደኛው ከምንም ቀጥታ በማምጣት (የመጀመሪያዎች «ምድር» እና ምናልባት ወፎች፥ በዚህ ምዕራፍ «ፈጠረ» የሚለው ግሥ በ1፥1 እና በ1፥21 ላይ ብቻ ይገኛል) ሲሆን፥ ሁለተኛው አስቀድሞ ከተፈጠሩት ነገሮች የሠራው ነው። «ፈጠረ» የሚለው ግሥ በተለይ የመጀመሪያውን የአፈጣጠር ዐይነት ሲያመለክት፥ «አደረገ» ሁለተኛውን ያሳያል። ይሁን እንጂ

«ፈጠረ» የሁለተኛውን የአፈጣጠር ዐይነትም ሊያመለክት ይችላል (ቊ. 26:27)፤ በአጠቃላይም የስድስቱን ቀን ሥራ ያመለክታል፤ ዘጸ. 20፥11።

3. እግዚአብሔር ሁሉን በቅደም ተከተል ፈጠረ፤ ይህም መጀመሪያ የሚታየውን በስድስቱ ቀኖች ላይ ባለው አጽንዖት በመገንዘብ ነው። በሚከተለው ንድፍ በየቀኑ የተሠራውን የእግዚአብሔርን የሥራ ቅደም ተከተል በይበልጥ ልናስተውል እንችላለን።




በመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀኖች እግዚአብሔር ብርሃንንና ጨለማን፥ ከጠፈር በታችና ከጠፈር በላይ ያሉትን ውሃዎች፥ የብስንና የውሃ ማከማቻውንም ለየ፤ ቊ. 4:7:10። በሁለተኛው ሦስት ቀኖች እግዚአብሔር የብርሃንን ዓለም፥ ሰማይንና ውሃውን፥ ምድርንም ሞላ፤ ቊ. 16:20-21:24-27።

በ3ኛውና በ6ኛው ቀኖች እግዚአብሔር ሁለት ርምጃዎችን ወሰደ። በ3ኛው ቀን እግዚአብሔር የብስን ከውሃዎች ከለየ በኋላ ለእንስሳትና ለሰው የሚሆኑ ዘርንና ፍሬን የሚሰጡ ተክሎችንና ዛፎችን አበቀለ፤ በስድስተኛው ቀንም እንስሳትንና ሰውን ፈጠረ።

በዚህ ዐይነት የስድስቱን ቀኖች ሥራ ስንመለከት እያንዳንዱ ሥራ ለሚከተለው መንገድ እንደከፈተ እናያለን፥ እንደዚሁም ሕያዋን ፍጡራን ሲፈጠሩ፥ ምግብ ተዘጋጅቶላቸው ነበር። እግዚአብሔር ሕይወትን ሲሰጥ ለዚያ ሕይወት አስፈላጊውን አስቀድሞ ያዘጋጃል።

አንዳንዶች በዚህ ንድፍ ያለውን አስተሳሰብ በመከታተል ስድስቱ ቀኖች የፍጥረትን ቅደም ተከተል ሳይሆን እግዚአብሔር ሁሉን እንደፈጠረ የሚያሳዩ ጸሐፊው የተጠቀመባቸው ዘዴዎች ናቸው ብለው ያምናሉ። ሌሎችም በቁሙ ባለ ሃያ አራት ሰዓት ስድስት ዕለታት እንደሆኑ አሳባቸውን ያጸናሉ። የተወሰኑት ደግሞ ስድስቱ ቀኖች ሃያ አራት ሰዓቶች ወይም ረጅም ዘመኖች ሳይሆኑ የፍጥረት «ስድስት» ሥዕሎች ወይም ስለ ፍጥረት ስድስት አመለካከቶች እንደሆኑ ያስባሉ። በዚህ አስተሳሰብ በማናቸውም በኩል ሲመረመር እግዚአብሔር ፍጥረትን ፈጥሮታል፤ ሰው ዋናው የፍጥረት ሥራ ነው፤ እግዚአብሔር ከፍጥረት ሁሉ በላይ ነውና በሰባተኛው ቀን በማረፉ ሰው የፈጣሪውን አርአያ ሲከተል፥ በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔርን ማምለክ አለበት። በዚህ ጽሑፍ አንድ ሊቅ፥ «እዚህ ላይ ለጊዜ ቅደም ተከተል ስፍራ የለም» ብሏል (7)።

ከዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ አተረጓጎም መላምቶች መካከል አንዱ የሆነው ይህ መላ ምት ልዩ ልዩ ችግሮችን፥ በተለይም ከዘመናዊ ሳይንስ የተነሣ የዓለምንና የሕያዋን ፍጡራንን የዕድሜ ግጭቶች ቢፈታም ከምዕራፉ ሂደት ጋር የሚስማማ አይመስልም።

ምክንያቱም 1ኛው ከ4ኛው፥ 2ኛው ከ5ኛው፥ 3ኛው ከ6ኛው ቀን ጋር እስከዚህ ድረስ አይገናኙም። ከዚህም በላይ ቍ. 1-2-3-4-5-6 ሰው ከሚጠቀምበት የሳምንት አጠራር ጋር ሲገናኙና 7ኛው ቀን የዕረፍት ቀን ሲሆን፥ የጊዜ ቅደም ተከተል እንደሚያሳይ የሚበዙቱ ያምናሉ። መላምቱን ከሚቀበሉት አንዳንዶች የጸሐፊው አቀራረብ፥ አንባቢዎቹ በሳምንት ቀኖች ለተፈጠረባቸው ነገሮች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ይፈልጋል ይላሉ። ይህ ጥሩ አሳብ ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን በቀኖቹ ውስጥ ለምስጋና ቢጠቀምም የቅደም ተከተልን አሳብ ግን አይነኩም፤ መዝ. 104፤ 136፥4-9።

ይህ መላምት የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነት ባይክድም፥ ለአተረጓጐሙ አስተማማኝ መሠረት ያለው አይመስልም። ሆኖም ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው፥ በስድስቱ ቀኖች የተፈጠሩ ነገሮች ቅደም ተከተል እግዚአብሔር በሥራው ያለውን ጥበብ ያሳያል።

4. እግዚአብሔር ሁሉን እንደ ወገኑ ፈጠረ፤ ዘፍ. 1፥11:12:21:24:25። እዚህ ላይ «ወገን» የሚለውን ቃል ትርጕም ለመወሰን ባንችልም ቢያንስ አራት ነገሮችን ማተት እንችላለን። ሀ) ከስንዴ ዘር ስንዴ፥ ከባሕር ዛፍ ፍሬ ባሕር ዛፍ፥ ከአሞራ አሞራ፥ ከበግ በግ ... ወዘተ ይገኛል። ሰው ሲፈጠር መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር «እንደ ወገኑ» ሰውን ፈጠረ አይልም፤ ምክንያቱም ሰው ሁሉ ከአንዱ ከአዳምና ከሔዋን ተገኝቷልና። ለ) አንድ ዐይነት ወገኖች ቢደባለቁ ብዙ አያፈሩም። ለምሳሌ ፈረስና አህያ ቢገናኙ በቅሎ ይወለዳል፤ በቅሎዎች ቢገናኙ ግን ምንም አይወለድም። ሐ) ሰው፥ እያንዳንዱን ፍጡር እንደ ወገኑ ሊጠቀምበት ይገባል፤ በምክንያት ተፈጥሯልና። መ) እግዚአብሔር እጅግ ብዙ ዐይነት ፍጥረት ፈጥሯልና ሰው በዚህ ብዛት ሊደሰት ይገባዋል። ለምሳሌ በዓለም ሦስት ሺህ የወፍ ዐይነት አለ፤ ከዚህም ውስጥ ስምንት መቶው በኢትዮጵያ ይገኛል። ብዙ የዛፍ ዐይነትም አለ፤ ከዚህም ውስጥ አንድ መቶው አዲስ አበባ በሚገኘው ብሔረ ጽጌ መናፈሻ ውስጥ ይታያል።

5. እግዚአብሔር ሁሉን መልካም አድርጎ ፈጠረ፤ እያንዳንዱን ነገር ሲፈጥር ወይም አንድ ነገር ሲያደርግ፥ እግዚአብሔር የሠራውን ያንኑ ነገር መልካም እንደሆነ አየ፤ ዘፍ. 1፥4:10:12:18 :21:25። መልካም ሲል የተሠራው የፈጣሪውን ዕቅድ የሚፈጽምና ለሌላ ነገር ዕንቅፋት እንደማይሆን ቢያንስ ያሳያል። እግዚአብሔር ሰውንም ከፈጠረ በኋላ «እግዚአብሔር ያደረገውን ሁሉ አየ፤ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ»፤ ቍ. 31። ይህንም ሲል፥ እያንዳንዱ ነገር በራሱ መልካም መሆኑን ብቻ ሳይሆን፥ ነገሮቹ ሁሉ በአንድነት ተገኝተው እርስ በርሳቸው ተስማምተው፥ ያለ ግጭት መኖር እንደሚችሉና ቢያንስ የእግዚአብሔርን ዕቅድ እንደሚፈጽሙ ያሳያል። ክፉት ወደ ዓለም በመግባቱ ይህን መረዳት ወይም የመጀመሪያው የሰባተኛው ቀን ሁኔታ ምን ያህል ክብርና ደስታ እንደነበረበት ማሰብ አንችልም። ፍጥረት የእግዚአብሔርን ደግነት አንጸባረቀ። የፀሐይን መውጣት ወይም መጥለቅ፥ የፍጥረትን ቀለሞች፥ የፈረስን አካሄድ፥ የአንበሳን ክብር፥ የእናትና ልጅን የእርስ በርስ ደስታ ... ወዘተ ስናይ፥ ስለዚያ ቀን ደስታና ክብር ትንሽ ፍንጭ ሊኖረን ይችላል።

6. እግዚአብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ ዘፍ. 1፥26። እግዚአብሔር ብዙ ዐይነት ሕያዋን ፍጡራንን ከፈጠረ በኋላ (ቍ.20-25)፥ ሰው ሲፈጠር ከሌሎች ፍጡራን ሁሉ ለየት ያለ መሆኑ ይታያል። «እግዚአብሔርም አለ ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር» ማለቱ ሰው ከመፈጠሩ በፊት ልዩ ምክር እንደነበረና ሰው በእግዚአብሔር መልክ እንደተፈጠረ ያሳያል። እግዚአብሔር ሌሎች ሕያዋን ፍጡራንን

ሲፈጥር፥ ተባትና እንስት አድርጎ እንደፈጠራቸው ግልጥ ቢሆንም አልተጻፈም። ሰው ሲፈጠር ግን «ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው» በማለቱ ከእንስሳት መብለጡን አሳየ። የወንዶችና የሴቶች እኩልነትም የሚታየው በእግዚአብሔር መልክ አብረው በመፈጠራቸው ነው። ከእንስሳት ሰውን እንዲለይ የሚያደርገው በእግዚአብሔር መልክ መፈጠሩ ነው። ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ተመሳሳይነትና ልዩነት መኖሩ ግልጥ ነው። ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ ዋነኛው ነገሩ ከእግዚአብሔር ጋር ልዩ ግንኙነት አለው፤ ይኸውም እግዚአብሔር ለሰው ይናገራል፤ ፈቃዱንም ይገልጥለታል (ቍ.28)። እንደዚሁም ከሌላ ፍጥረት ይልቅ ሰውን በመመልከት የእግዚአብሔርን ባሕርይ በመጠኑ ማስተዋል ይቻላል። ሰውም በመልኩ በመፈጠሩ አርአያውን፥ በተለይ ስድስት ቀን ሠርቶ በሰባተኛው ማረፉን መከተል እንደሚገባው እንገነዘባለን። «ትምህርተ ሰብእ» በሚለው በ4ኛው ጥናት የእግዚአብሔር መልክ በሰዎች ላይ እንዴት እንደሚታይ በዝርዝር ለማብራራት እንሞክራለን።

7. እግዚአብሔር ሰውን የፍጥረት ሁሉ የበላይ አድርጎ ፈጠረው፤ ዘፍ. 1፥28-30። እግዚአብሔር ሰዎችን ሲፈጥር ባረካቸው፤ በረከቱ የሚታየውም ከፍ ያለ ኀላፊነትና ሥራ ለእነርሱ በመስጠቱ ነው። እነርሱ በመባዛት ዓለምን መሙላትና መግዛት ነበረባቸው። ዓለምን ሲገዙ በሌሎች ሕያዋን ፍጡራን ላይ ለመሠልጠን ታዘዙ።

ይህን ትእዛዝ ሲፈጽሙ ትልቅ መብት ተሰጥቷቸው ነበር፤ ይኸውም የተክሎችንና የዛፎችን ዘርና ፍሬ በየዐይነቱ በምግብነት መጠቀም ነበር። እግዚአብሔር ሕይወትን ሲሰጥ ለፍጥረቱ በቂ ምግብ ያዘጋጃልና ፍጡራን እንደ ተፈጥሮአቸው ዘር ወይም ፍሬ በልተው ይጠግባሉ። ሰው ግን ዘርና ፍሬ በየዐይነቱ እንደፈለገ ሊመገብ ይችላል፤ ብዙ ዐይነት ሲበላ ባለመሰልቸቱ ይደሰታልና። የእግዚአብሔር ልግስና በዚህ ይገለጥለታል።

ሰው ፍጥረትን ሲመለከት ቢያንስ ስለ ሦስት ነገሮች ሳያስብ አይቀርም።

ሀ) ምሥጢር አለበት፤ በተለይ ስለ ሁለት ነገሮች፤ 1ኛው እግዚአብሔር እንዴት እንዳደረገው፤ 2ኛው የድጋፍ ኑሮው ነጻ መሆንና አመክንዮታውያን ፍጡራን (ሰዎችና መላእክት) እግዚአብሔርን እየወደዱ በመታዘዝ ወይም እግዚአብሔርን ንቀፈው ራሳቸውን እንደ አማልክት በመቍጠር ነጻና ግብረገባዊ ምርጫዎችን ማድረግ እንዴት እንደሚችሉ ነው።

ለ) ጊዜና ስፍራ ከፍጥረት ጋር የተያያዙ ናቸው፤ በእግዚአብሔር «ውስጥ»አይደሉም፤ ሆኖም ስፍራዎች ሁሉና ጊዜያት ሁሉ ሁልጊዜ በፊቱ ናቸው፤ ም.23ሐ ይመ.።

ሐ) እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር፥ በኋላ በዓለም ውስጥ ገብቶ አዲስ ሥራ መሥራት እንዳይችል አላደረገም። ዓለም ማኅተም እንደታተመበት ሣጥን አይደለም። እግዚአብሔር ሲፈጥር በቃሉ ተናገረ፤ እንደገናም በዓለም መናገር ይችላል። ተአምራትን ሊያደርግ ይችላል። የሰዎችን ፈቃድ ሊቀሰቅስ ይችላል፤ የዓለምንም ታሪክ ወደሚፈቅድበት አቅጣጫ ሊመራ ይችላል። እግዚአብሔር በዓለም አሁን አዲስ ነገርን ቢፈጥር፥ ከፈተኛው ነገር ወይም ሁኔታ ምን ያህል እንደሚወጣ ለማወቅ አንችልም፤ ይህም የሚሆነው ነገሩን ራሱ ካልገለጠልን ነው (8)።

እንግዲህ አራት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ብዙ ትምህርትን ሲሰጥ፥ በዚህ ዓለም ውስጥ ሰው ስላለው ልዩ ስፍራ፥ ስለ ጥሪው፥ ስለ

ኅላፊነቱና ስለ መብቱ ብዙ ያስተምራል። ሰው በፍጥረት እንዴት መጠቀም እንደሚገባው በምዕራፍ 32 በይበልጥ እናትታለን።

## ሐ) የፍጥረት ታሪክ ትርጉም በመጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ጥቅሶች ስለ ፍጥረት ይናገራል፤ ጸሐፊዎቹም፥ አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን እንደ እውነተኛ ታሪክ ሲቀበሉት በልዩ ልዩ ትምህርት ላይ ያተኩራሉ። እነዚህን ጥቅሶች እንደ አጽንዖታቸው መርጠን እንደሚከተለው ልንዘረዝራቸው እንችላለን (9) ፦

1. እግዚአብሔር ሁሉን ስለ መፍጠሩ፤ «በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፤ ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ ... እርሱ ተናግሯልና፤ ሆኑም፤ እርሱ አዘዘ፤ ጸኑም» በማለቱ እግዚአብሔር በቃሉ ሰማያትንና በሰማያት ያሉትን ሁሉ መፍጠሩን አረጋግጧል፤ መዝ. 33፥6:9። እንደዚሁም በአዲስ ኪዳን «የሚታዩትና የማይታዩትም ... በሰማይና በምድር ያሉት ሁሉ በእርሱ (በክርስቶስ) ተፈጥረዋል» ሲል ከ«ሁሉ» ውጭ አንድም ነገር እንደሌለ ያሳያል፤ ቆላ. 1፥15-16። ዮሐንስ 1፥3፥ የሐዋርያት ሥራ 4፥24፤ 17፥24 እና የዕብራውያን መልእክት 11፥3 ይህን ያሳያሉ።

2. በፍጥረት ሥራ ላይ ስለ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት፤ «እነሆ፥ ተራሮችን የሠራ፥ ነፋስንም የፈጠረ፥ የልቡንም አሳብ ለሰው የሚነግር፥ ንጋትን ጨለማ የሚያደርግ፥ በምድርም ከፍታዎች ላይ የሚረግጥ፥ ስሙ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው»፤ አሞጽ 4፥13፤ ኢሳ. 40፥26:28።

3. ከፍጥረት ሁሉ በላይ እግዚአብሔር ታላቅ ስለመሆኑና ስላለመወሰኑ፤ «ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም»፤ ሐ.ሥ. 17፥24፤ መዝ. 90፥2፤ 102፥26:27።

4. በፍጥረት ሥራ ስለታየው የእግዚአብሔር ጥበብ፤ «ምድርን በኃይሉ የፈጠረ፥ ዓለሙንም በጥበቡ የመሠረተ፥ ሰማያትንም በማስተዋሉ የዘረጋ እርሱ ነው ...»፤ ኤር. 10፥12-16፤ ኢሳ. 40፥12-14፤ ዮሐ. 1፥3።

5. ስለ እግዚአብሔር ልዕልናና ስለ ፍጥረቱ ግብ፤ «በስሜ የተጠራውን ሁሉ፥ ለክብሬ የፈጠርሁትን፥ ያበጀሁትንና የሠራሁትን አምጡ»፤ ኢሳ. 43፥7 አ.መ.ት.፤ ራእ. 10፥6።

6. በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ የፍጥረት ሥራው መሠረታዊ ሥራ ስለ መሆኑ፤ «እርሱ (ክርስቶስ) ... ከፍጥረት ሁሉ በፊት በኵር ነው፤ ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯል፤ በሰማይና በምድር ያሉ፤ የሚታዩና የማይታዩ፥ ዙፋናት ቢሆኑ ወይም ኃይላት፥ ገዦች ቢሆኑ ወይም ባለ ሥልጣናት፥ ሁሉም ነገር በእርሱና ለእርሱ ተፈጥሯል»፤ ቆላ. 1፥16 አ.መ.ት.፤ 1ቆሮ. 11፥9።

7. የተፈጠሩ ሁሉ እግዚአብሔርን ማምለክ የሚገባቸው ስለ መሆኑ፤ «አንተ ብቻ እግዚአብሔር ነህ፤ ሰማዩንና የሰማያት ሰማይን ሠራዊታቸውንም ሁሉ፥ ምድሩንና በእርሷ ላይ ያሉትን ሁሉ፥ ባሕሮቹንና በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ ፈጥረሃል፤ ሁሉንም ሕያው አድርገኸዋል፤ የሰማዩም ሠራዊት ለአንተ ይሰግዳሉ»፤ ነህ. 9፥6፤ ሮም 1፥25፤ ራእ. 4፥10-11።

8. ሰው የፍጥረትን ትምህርት መቀበል የሚገባው በእምነት ስለ መሆኑ፤ «ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደተዘጋጁ፥ ስለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ

በእምነት እናስተውላለን»፤ ዕብ. 11፥3። የአብርሃም የእምነት ጉዞ ሲተረክ፥ እግዚአብሔር «የሌለውንም እንዳለ» ወይም «ያልነበረውን እንደነበረ» የሚያደርግ አምላክ መሆኑ ተገልጧል፤ የባሕርዩ መገለጫ የሆነው ይህ ክህሎቱም ፍጥረትንም ሆነ ሌላ ነገርን ሊያመለክት ይችላል፤ ሮም 4፥17።

ዓለም ከቍሳዊ ነገር አለመፈጠሩን በሚከተለው ምዕራፍ እናትታለን።

## መ) የቅድስት ሥላሴ ሥራ በፍጥረት

እግዚአብሔር ሁሉን በመፍጠሩ ከጣዖታት ይለያል፤ መዝ. 96፥5፤ ኢሳ. 37፥16፤ ኤር. 10፥11-12። ትምህርቱንም ስንመረምር የአብ፥ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በፍጥረት መታየቱ በመጽሐፍ ቅዱስ ይገኛል።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ዓለም ጣዖታት ከንቱነት ከጻፈ በኋላ፥ «... ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ (ከእግዚአብሔር) የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፤ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን» በማለቱ በፍጥረት አብ በተለይ ሲታይ፥ ወልድ በፍጥረት አብሮ እንደሠራ ያሳያል፤ 1ቆሮ. 8፥6። በፍጥረት ሥራ ወልድ ያለው ተሳትፎ በልዩ ልዩ ጥቅሶች ተጽፎ ይገኛል፤ ዮሐ. 1፥3፤ ቆላ. 1፥15-17። መንፈስ ቅዱስም በፍጥረት ሥራ መሳተፉን ከብሉይ ኪዳን ጥቅሶች ማስተዋል እንችላለን፤ ዘፍ. 1፥2፤ ኢዮብ 26፥13፤ 33፥34፤ መዝ. 104፥30፤ ኢሳ. 40፥12-13። የፍጥረት ሥራው ለሦስቱ አካላት አልተከፋፈለም፤ ሆኖም ጠቅላላው የፍጥረት ሥራ በእያንዳንዱ አካል እንደተፈጸመ ይታሰባል። ከአብ፥ በወልድ አደራጅነት፥ በመንፈስ ቅዱስ ፈጻሚነት ተከናውኗል ማለት ይቻላል፤ ም. 26ለ፤ ም.26 ሐ3።

በምዕራፍ 27ሐ ስለ ቅድስት ሥላሴ ምሳሌዎች ስናትት በፍጥረት ውስጥ ብቃት ያለው ምሳሌ አለመገኘቱን አይተናል። ሆኖም በፍጥረት ሦስትነትን በብዙ አቅጣጫ እናያለን። ለምሳሌ፥ ስፍራ በርዝመት፥ በስፋትና በቁመት ይለካል። ጊዜ ያለፈ፥ የአሁንና የወደፊት ነው። ሰውንም ስንመለከት አካልነቱ በአእምሮ፥ በስሜትና በፈቃድ ይወሰናል። በመጽሐፍ ቅዱስም ሰዎች ሁሉ በኖኅ ሦስት ልጆች በሴም፥ በካምና በያፌት ይከፈላሉ፤ የመገናኛ ድንኳኑም ሦስት ክፍሎች አሉት፤ እነርሱም የውጭ አደባባይ፥ ቅድስትና ቅድስተ ቅዱሳን ናቸው። ስለ እግዚአብሔር ለሰዎች ሦስት ዐይነት ምኞት አላቸው፤ አንዳንዶች ከሁሉ በላይ የሚነግሠውን፥ ሌሎች አጠገባቸው የሚገኘውን፥ የተወሰኑት ደግሞ በውስጣቸው የሚኖረውን ይፈልጋሉ። እያንዳንዱ ሃይማኖት ከሦስቱ በአንዱ ላይ ሲያተኵር በክርስትና ሦስቱም በፍጹምነት ይገኛሉ።

እነዚህ የሦስትነት ምሳሌዎች ቅድስት ሥላሴ እንዳለ አያረጋግጡም፤ ሆኖም ፍጥረት የሥላሴ ምግባር በመሆኑ፥ በሥራው የሦስትነትን ፍንጮች በማየታችን ትምህርታችን አመክንዮታዊ መሆኑን እንገነዘባለን።

### ማስታወሻ

(1) «የአሪት ጸሐፊ» በመቅመቃ. ይመ.

(2) ለምሳሌ ERICH SAUER በ THE DAWN OF WORLD REDEMPTION ገጽ 34-36። እዚህ ላይ የSAUER አስተሳሰብ በእንግሊዝኛ GAP THEORY ይባላል።

(3) GRUDEM ገጽ 287-289 ይመ.

(4) «ያለው ሁሉ እግዚአብሔር ነው» የሚለው አሳብ በእንግሊዝኛ ቋንቋ PANTHEISM ይባላል።

(5) እግዚአብሔርና ግዙፉ ዓለም ከዘለዓለም «አብረው አሉ» የሚለው አሳብ በእንግሊዝኛ DUALISM ይባላል።

(6) «ያለው ሁሉ ፍጥረት ብቻ ነው» የሚለው አሳብ በእንግሊዝኛ MATERIALISM (ቍሳዊነት) ይባላል።

(7) HENRI BLOCHER በ IN THE BEGINNING ገጽ 52። ስለዚህ አሳብ GRUDEM ገጽ 300-304 ይመ.።

(8) «እግዚአብሔር ዓለምን ከፈጠረ በኋላ ከዓለም ርቆ የሚገኝ በመሆኑ በዓለም ውስጥ አሁን ምንም አይሠራም» የሚለው ትምህርት በእንግሊዝኛ DEISM ይባላል።

(9) ይህ ዝርዝር በ BERKHOF ገጽ 127-128 ላይ የተመሠረተ ነው።

# ምዕራፍ 31 - ስለ ፍጥረት የእግዚአብሔር አስተርእዮ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ(1)

ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ሲጻፍ የእስራኤል ሕዝብ ፍጥረትን በተመለከተ ከሚጎራበቱት ሕዝቦች አስተሳሰብ እንዲጠበቅ ለማስጠንቀቅ መጻፉን አስቀድመን አይተናል። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ የአበው ልዩ ልዩ አተረጓጐም ቢኖርም፥ ዋናው ትግል ከዘመናዊ ሳይንስ ትምህርት ጋር ነው። ክርስቲያን የሳይንስን ትምህርት እንዴት መመልከት እንደሚገባው በምዕራፍ 8ሀ አትተናል። ክርስቲያኖች ስለ ሳይንስ ትምህርት ሲሰሙ፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር እንዲያዛምዱት አተረጓጐማቸውን እንደገና መረመሩ፤ አንዳንዶችም አስተሳሰባቸውን ቀየሩ። ክርስቲያን አተረጓጐሙን ስለ አንዳንድ ጥቅስ ቢለውጥ፥ እምነቱን ካደ ወይም መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል አለመሆኑን አመነ ማለት አይደለም። ለምሳሌ አንድ ሊቅ በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያምን ክርስቲያን የሚከተሉትን አሳቦች መቀበል እንደሚችል ጽፏል :-

1. እግዚአብሔር በዐጭር ጊዜ የፈጠረውን ዓለም፥ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት እንደተፈጠረ አስመስሎ ማሳየቱን፥

2. በኦሪት ዘፍጥረት 1፥1 እና 1፥2 መካከል፥ ወይም በ1፥2 እና 1፥3 መካከል ረጅም ዘመን መኖሩን፥

3. በፍጥረት ታሪክ ቀን ረጅም ዘመንን የሚያመለክት መሆኑን፥

4. የጥፋት ውሃ የምድርን ድንጋዮች አቀማመጥ በመገልበጥ የሳይንስን ምርምር ዋስትና የሌለው እንዳደረገው፥

5. በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ የ«ዐይነት» አጠቃቀም እጅግ ሰፊ መሆኑን፥

6. ከሰው ውድቀት በፊት እንስሳት ይሞቱ እንደነበር።

ሊቁ እንደዚህ ሲል እርሱ ራሱ እነዚህን አሳቦች የሚቀበል መሆኑን መግለጡ ሳይሆን፥ አንድ እውነተኛ ክርስቲያን ከእነዚህ ነጥቦች አንድን ወይም ሁሉን ቢቀበል፥ ከትክክለኛ ትርጉም ወጥቷል ማለት የማይገባ መሆኑን ያስተምራል፤ ምክንያቱም በእነዚህ ነጥቦች የፍጥረት ታሪክ ግልጥ ሆኖ የሚታይ ባለመሆኑ ነው። በዚህ ምክንያት አንድ አማኝ የሳይንስ ትምህርት አመክንዮታዊ ቢመስለው፥ ስለ ፍጥረት ወዳልተለመደ አተረጓጐም ሊያዘነብል ይችላል (2)።

እንግዲህ ቍሳዊው ዓለም በፈጣሪያችን ስለተፈጠረ ያለ ፍርሀት መጽሐፍ ቅዱስን በጋለ መንፈስ ስናጠና፥ ከእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛ ትርጉም ጋር ግጭት እንደማይኖር ማመን ይገባናል። በዚህ መንፈስ የሚከተሉትን ነጥቦች እናትታለን።

## ሀ) የዓለም ህልውና

መጽሐፍ ቅዱስ፥ የዓለምን ህልውና እንዴት እንደሚገልጠው በምዕራፍ 30 ለማሳየት ሞክረናል። ትምህርቱ በዐጭሩ እግዚአብሔር ሰማያትንና ምድርን ለራሱ ክብር ከምንም መልካም አድርጎ ፈጠራቸው የሚለው ነው። ሰው ይህን ማወቅ የሚችለው በእምነት ብቻ ነውና በሌላ መንገድ ሲሄድ ወደ ችግሩ ጕድጓድ መውደቁ አስገራሚ አይደለም፤ ዕብ. 11፥3። ይህን ትምህርት የማይቀበሉ ሰዎች ሦስት ዐይነት አሳብ ሊኖራቸው ይችላል።

1. ዓለማት ሁሉ ከዘለዓለም ናቸው። መጀመሪያ አልነበራቸውም፤ ቢለዋወጡም ፍጻሜ የላቸውም። ይህን አሳብ ይዞ ሰው አንድ ዐይነት አምላክ እንዳለ ቢያስብ፥ ይህ «አምላክ» ፈጣሪ ባለመሆኑ ሁሉን አይገዛም፤ በእርሱና በቍሳዊው ዓለም መካከል ግጭት ሊኖር ይችላል፤ ለወደፊትም በሚሆነው ላይ ምንም ዋስትና የለም።

2. ዓለማት ሁሉ በድንገት «ተገኙ»። እንደዚህ ከሆነ የሰው አእምሮ ከየት መጣ? ከምንም መምጣቱን ማሰብ የሚጠይቀው እምነት እንዴት ያለ ይሆን!

3. ከዓለማት መገኘት በፊት አንድ ነገር፥ አንድ ኀይል ነበረና ዓለማት ድንገት መጡ። ብዙ ሰዎች፥ በተለይ በሳይንስ የሚያምኑ ፈጣሪ አምላክ እንዳለ ማሰብ አይፈልጉም፤ በዚህ አሳብ ደስ አይሰኙም። ደግሞም አሳቡ ጥያቄ ያስነሣል፤ ይኸውም ይህ «ነገር» ወይም ይህ «ኀይል» ከየት መጣ ወይስ እንዴት ተገኘ? የሚል ይሆናል።

በዚህ የሞኝነት አስተሳሰብ ፈንታ (መዝ. 14፥1) ሁሉ በክርስቶስ፥ በጥበቡ፥ በእውነቱ፥ በፍቅሩ መፈጠሩ እንዴት ያለ አርኪ አሳብ ነው!፤ ዮሐ. 1፥3፤ ዕብ. 1፥2። ሁሉ የእርሱ ሥራ ነውና በትሥጉቱ ወደዚህ ዓለም ገባ፤ በትንሣኤውም የተፈጠረውን ወደ ሰማያት ይዞ በመሄድ በፊቱ የእግዚአብሔርን ክብር እናያለን፤ 2ቆሮ. 4፥6።

ለ) የዓለም ዕድሜ

የብሉይ ኪዳን ትውልድ ሐረጎችን በመመርመር የአየርላንድ ሊቀ ጳጳሳት ያዕቆብ ሁሸር (1581-1656) ዓለም የተፈጠረው በ4004 ዓመት ከክርስቶስ በፊት እንደሆነ አሰበ። በኢትዮጵያ በሌላ አቈጣጠር ዓለም የተፈጠረበት ጊዜ 5500 ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት እንደሆነ ሲታሰብ ቈይቷል። የሳይንስ ምርምር ውጤት የዓለም ዕድሜ 4400 ሚሊዮን ዓመታት እንደሆነ፥ ደግሞም ከሁሉ ርቆ የሚገኘው ኮከብ ብርሃን ወደ እኛ ለመድረስ በሚፈጀው 8000 ሚሊዮን ዓመት ሊለካ እንደሚችል ያሳያል። ይህም የምናየው ከ8000 ሚሊዮን ዓመታት በፊት የሆነ ነገር ነው ማለት ይሆናል። እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስን ከሳይንስ ጋር እንዴት ማዛመድ ይቻላል? ምንስ ሙከራ ተደርጓል? (3)

1. የሳይንስ አቈጣጠር ልክ አይደለም ማለት ነው። ሳይንስ ሊሳሳት ይችላል። ሆኖም በሳይንስ ምርምር ውስጥ ብዙ ነገር ተገኝቷልና ከተገኘው የምርምር ውጤት የተነሣ ብዙ አስገራሚ ነገሮች በቴሌቪዥን፥ በኮረንቲ፥ በሕክምና በሌላም መስክ እየተሠሩ ስለሚታዩ፥ የሳይንስ አቈጣጠር ስለ ዓለም ልክ አይደለም ማለት አመክንዮታዊ አይመስልም።

2. በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ «ቀን» ሲል ሃያ አራት ሰዓትን ሳይሆን ረጅም ዘመንን ያመለክታል። ሰዎች ለዚህ ትርጒም ልዩ ልዩ ማስረጃ ያቀርባሉ።

ሀ) ይህ አተረጓጐም ከዘመናዊ ሳይንስ ጊዜ ተነሥቶ ሳይሆን ከአበው ጀምሮ የታወቀ ነው። አተረጓጐሙ ከቅዱስ አውግስጢኖስ በፊት የሚታወቅ ሲሆን፥ ከእርሱ በኋላ ከአበው መካከል የሚበዙቱ ይቀበሉት ነበር።

ለ) አንቀጹን ስንመረምር ፀሓይ ከመፈጠሯ በፊት ሦስት ቀናት ዐልፈው ነበርና በእነዚያ የመጀመሪያ ቀናት ሃያ አራት ሰዓት እንዴት ይለካ ነበር? ብለን መጠየቅ እንችላለን። ደግሞም «እግዚአብሔር አምላክ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረ ቀን» ሲል ቀን ጠቅላላውን የፍጥረትን ጊዜ ያመለክታል፤ ዘፍ. 2፥4። በሌሎች ጥቅሶች «ቀን» ሲል ዘመንን ወይም ረጅም ጊዜን ያመለክታል፤ ለምሳሌ የቍጣው ቀን (ኢዮብ 20፥28)፥ የመከራ ቀን (መዝ. 20፥1)፥ የጦርነት ቀን (ምሳ. 21፥31)፥ መልካም

ቀንና ከፉ ቀን (መክ. 7፥14)፥ የመዳን ቀን (2ቆሮ. 6፥2) የታወቁ ናቸው። ሆኖም ሰው ቀን ሲል ብዙ ጊዜ አሳቡ ሃያ አራት ሰዓትን የሚያመለክት ነውና ስለ ሳይንስ ሳያውቅ አሪት ዘፍጥረት ስለ ስድስት ተከታታይ ሃያ አራት ሰዓት ቀኖች የሚናገር ይመስለዋል። በዚህ አሳብ ውስጥ ሆኖ ሲያነቢ ወደ አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ ግብ ይደርሳል። GRUDEM ገጽ 293-300።

3. በምዕራፍ 1፥1 እና 1፥2 መካከል ረጅም ዘመን እንደነበረ የሚያስተምሩ አሉ፤ ሆኖም ይህ አስተሳሰብ ከአንቀጹ ጋር ብዙ የሚስማማ አለመሆኑን በምዕራፍ 30 ሀ1 አሳይተናል።

4. እግዚአብሔር በዐጭር ጊዜ የፈጠረውን ዓለም፥ በብዙ ሚሊዮን ዓመታት የተፈጠረ አስመሰለው። ለምሳሌ አዳም በተፈጠረበት ቀን እንደ ሕፃን ሳይሆን እንደ ሠላሳ ዓመት ሰው ሆኖ ተፈጠረ፤ ሔዋንም በተፈጠረችበት ቀን ሙሉ ሴት ነበረች። እግዚአብሔር ዓለምን ሁሉ በዚህ መንገድ መፍጠር ይችላል፤ እንደዚሁም መጀመሪያ የተፈጠረው ዶሮ ወይስ ዕንቁላል? የሚል ጥያቄ አለ፤ ነገር ግን ዓለማት ሁሉ ከብዙ ዘመናት ምልክቶችና ከቅሪተ አካላት ጋር አብረው እንደተፈጠሩ የሚያሳዩ ፍንጮች በመጽሐፍ ቅዱስ አናገኝም። እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር የሞቱትን እንስሳት መፍጠሩ ሰዎችን ለማታለል አይመስልምን? እንደዚሁም ይህ «እጅግ መልካም» እንደሆነ መናገር አይከብድምን? GRUDEM ገጽ 304-306።

5. አንዳንድ ሰዎች የጥፋት ውሃ በምድር ላይ ብዙ ለውጥ ቢያስከትልም፥ የሥነ ምድር ተመራማሪዎች የጥፋት ውሃ ያስከተለውን ውጤት ባለማስተዋላቸው ስለ ዓለም ዕድሜ ተሳስተዋል (4)። ኖኅ ከመርከብ ሲወጣ ዓለምን እጅግ ተለውጦ አላገኘውምና ለዚህ አስተሳሰብ በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ያለው አይመስልም። GRUDEM ገጽ 306-307።

6. የአሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድ አጻጻፍ እጅግ ውስብስብነት ያለው ነውና የቀናት ብዛትና ቅደም ተከተል የመጽሐፉን መልእክት ያብራራሉ እንጂ መልእክቱን ራሱን አያሳዩም (5)። አንድ ሊቅ፥ «የቀኖች ርዝመት» ምን ያህል ነበረ? ብለን ጸሓፊውን ብንጠይቅ ኖሮ በጥያቄው ግራ ይጋባ ነበር፤ ምክንያቱም የአጻጻፉ ዓላማ ሳይንስን ማስተማር ሳይሆን የእግዚአብሔርን አንድነትና ታላቅነት፥ ዓለም በቀውስ ሳይሆን በሥርዐት የተፈጠረ መሆኑን፥ ፀሓይና ጨረቃ አንበሪዎችም በእግዚአብሔር በመፈጠራቸው አማልክት አለመሆናቸውን ማሳየት ነበረ (6)። ከአጻጻፉ የተነሣ የተሰጠውን ሌላ ትርጒም በም. 30 ለ3 አትተናል።

መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሚቀበሉት በተለይ በሁለት አሳቦች መካከል ይከፈላሉ። የ«አሮጌ ምድር» ተከታዮች የተባሉ አንዳንዶች የሳይንስን የምርምር ውጤት ተቀብለው ከዚህ በላይ በቍጥር 2፥ በቍጥር 3 ወይም በቍጥር 6 በተጻፉት መሠረታውያን አሳቦች ይመራሉ። የ«አዲስ ምድር» ተከታዮች የተባሉት ደግሞ ዓለም በ10000ና በ20000 ዓመት እንደተፈጠረ አምነው አሳባቸውን ከዚህ በላይ በ1ኛ፥ በ4ኛና በ5ኛ ቍጥሮች በተጻፉት መሠረታውያን አሳቦች ይመራሉ (7)። ይህም ከሰው ዕድሜ ጋር የተያያዘ ነውና በሚከተለው ክፍል ማብራሪያ እንሰጥበታለን።

## ሐ) የሰው ዕድሜ

በስድስተኛው ቀን እንስሳትና ሰው ተፈጠሩ። ይህ ቀን ሃያ አራት ሰዓት ከሆነ፥ እንስሳት ከሰው ውድቀት በፊት አልሞቱምና ሞት በእንስሳት መካከል የገባው ከሰው ውድቀት የተነሣ ነው ማለት ይቻላል። በሰው ኀጢአት ምክንያት የአትክልት ዓለም

ተረገመ፤ ዘፍ. 3፥17-18። ከዚህም የተነሣ «ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ» በመኖሩ ሞት በሰው ላይ ብቻ ሳይሆን በእንስሳትም ላይ ደርሷል የሚሉ አሉ፤ ሮም 8፥19-23። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሞት ሲናገር በኀጢአት ምክንያት በሰው ላይ መድረሱን እንጂ ስለ እንስሳት ሞት አይናገርም፤ ዘፍ. 2፥17፤ 3፥17-19፤ ሮም 5፥12።

የፍጥረት ቀኖች ረጅም ጊዜያት ከሆኑና እንስሳት በረጅም ጊዜ ከሰው በፊት ከተፈጠሩ፥ እንስሳት ከሰው ውድቀት በፊት ሞቱ፤ በዚህም ምክንያት ቅሪተ አካላታቸው በብዙ ስፍራ ተገኝተዋል። እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር እንስሳትን ሲፈጥር፥ እያረጁ እንዲሄዱና እንዲሞቱ የወሰነ ይመስላል፤ ይህን አሳብ የሚያፈርስ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ አይገኝም፤ እንደዚህ ነውም ማለት አይቻልም። ሌላም አሳብ አለ፤ ይኸውም ቅሪተ አካላት የተገኙት በጥፋት ውሃ ጊዜ ከሞቱ እንስሳት ነው፤ ሆኖም ከምርምሩ ጋር ባለመስማማቱ የሳይንስ ተመራማሪዎች ከዚህ መላምት ጋር አይስማሙም።

በክብደት ተልቆ ከሚገኘው ከዝሆን ይልቅ ከፍ ያሉ ግዙፍ እንስሳት ቅሪተ አካላት በልዩ ልዩ ቦታ ተገኝተዋል። እንስሳቱ ከሰው በፊት የሞቱ ይሆናሉ፤ ወይም ከሰው ጋር አብረው የኖሩ ከሆኑ፥ በጥፋት ውሃ የሞቱና ተርፈው የቀሩ ናቸው የሚል ሁለት አስተሳሰብ አለ። እነዚህ እንስሳት በእንግሊዝኛ DINOSAURS ይባላሉ። እንደ ዘመኑ የሳይንስ ሊቃውንት ምርምር እነዚህ ትልልቅ እንስሳት ከ65 ሚሊዮን ዓመታት በፊት የጠፉ ናቸው።

የዓለምን ሁኔታ የሚመረምሩ የሳይንስ ሊቃውንት በሚከተለው አኳኋን ሰዎችን እንዳገኙ ይናገራሉ :-

- በመሣሪያ የሚጠቀምን ሰው ከ2-3.5 ሚሊዮን ዓመታት በፊት (እርሱ በድንጋይ መሣሪያዎች ተጠቀመ)

- ቀጥ ብሎ የሚቆምን ሰው ከ1.5 ሚሊዮን ዓመታት በፊት (በልዩ ልዩ ዐይነት ድንጋይ ተጠቀመ፤ ከ500000 ዓመታት በፊት በእሳት ተጠቀመ፤ ትልልቅ እንስሳትን ዐደነ)

- ጠቢብን ሰው ከ40000-150000 ዓመታት በፊት (እርሱ ሙታናቸውን ቀበረ)

- ጠቢበ ጠቢባን ሰው ከ18000-35000 ዓመታት በፊት (በዋሻዎች ሥዕሎችን ሣለ፤ ከብቶችን አረባ፤ ዕርሻን ዐረሰ፤ ብረታ ብረትን ሠራ)።

ይህን ስንመረምር እነዚህ «ሰዎች» አሁን እንዳሉት ሰዎች ናቸው ማለት አያስፈልግም። ለምሳሌ አንዳንድ እንስሳት በመሣሪያዎች ይጠቀማሉ፤ አንድ ፍጡር ሬሳ ቢቀብር፥ ሰው ነው አያሰኝም፥ በሳይንስ ተመራማሪዎች መካከል ልዩ ልዩ አስተሳሰብ አለ። አንዳንድ ሥዕሎች በዋሻ ሲገኙ በአንድ ዘዴ ከ20000-35000 ዓመታት በፊት እንደተሣሉ፥ በሌላ ዘዴ ደግሞ ከ11000 ዓመታት በፊት እንደተሣሉ ተገምቷል። እዚህ ላይ እንግዲህ የሳይንስ ተመራማሪዎች ስለ አንድ ነገር ሲናገሩ የተለያየ አሳብ ሊኖራቸው እንደሚችል ይታያል። ሆኖም የአሮጌው ምድር ወገኖችም ሆኑ የአዲስ ምድር ተከታዮች እነዚህ ሥዕሎች አሁን በሚኖሩ ሰዎች እንደተሠሩ ይስማማሉ። GRUDEM ገጽ 291-292።

እንግዲህ በዓለም የሚኖሩ ሰዎች ቢያንስ ከ12000 ዓመታት በፊት ከተገኙት ሰዎች ውስጥ የመጡ በመሆናቸው ብዙዎች እንደሚስማሙ እናያለን። አንባቢ በዚህ አሳብ ተስማማም አልተስማማም ዋናው ክርክር ወደተነሣበት ወደ ሰው አመጣጥ መሄድ ያስፈልጋል።

## መ) የሰው አመጣጥ

ቻርለስ ዳርዊን (CHARLES DARWIN) በ1859 ዓ.ም. "THE ORIGIN OF SPECIES BY MEANS OF NATURAL SELECTION" የሚለውን መጽሐፍ ካሳተመው ወዲህ ስለ ሕይወት፥ ስለ እንስሳትና ስለ ሰው አመጣጥ ብዙ ክርክር ተነሥቶ ቈይቷል። ዋናው የተቃውሞ ክርክር በመጀመሪያ የተነሣው በክርስቲያኖች ነበረ፤ ምክንያቱም ከኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 1-3 ጋር የዳርዊንን አሳብ ለማዛመድ እጅግ አስቸጋሪ ነው። በሳይንስ ዓለም ከሚገኙት ምሁራን የሚበዙቱ የዳርዊንን አሳብ ቢቀበሉም፥ በሙሉ ወይም በከፊል የማይቀበሉት ጥቂቶች አይደሉም። ከዚህም ጭቅጭቅ ሁሉ የተነሣ ብዙ መላምቶች ተበጅተው ይገኛሉ። ነገሩን በሚገባ ለማስተዋል የአዝጋሚ ለውጥ መሠረታዊ አሳብ ምን እንደሆነ መረዳት ይገባናል።

ከጥንት ጀምሮ ሕይወት ከየት መጣ? ለሚለው ጥያቄ ብዙ የመላምት መልሶች አሉ። እንደ ዳርዊን አሳብ ከዕለታት አንድ ቀን ልዩ ልዩ ዐይነት ቍሳዊ ነገሮች ተገናኝተው እንዲሁ በራሳቸው አንድ ነጠላ ሕያው ሴል (cell) ሆኑ። ይህ ሴል ራሱን እያበዛ ሴሎቹ ከጊዜ በኋላ ወደ አዲስ ዐይነት ሴሎች ተለወጡ። እነዚህ ለውጦች ውስብስብ ዕድገት ያለበት ልዩ ልዩ ሕይወት አመጡ። አካባቢው ተስማሚ ሲሆን፥ እነዚህ የሕይወት ዐይነቶች እየበዙ ሄደው የበለጠ ውስብስብነት ያለበትን የሕይወት ዐይነት አስገኙ፤ አካባቢው ተስማሚ ሆኖ ሳይገኝ ግን ጉድለት ያለበት የሕይወት ዐይነት ጠፋ። በዚህ ዐይነት ሂደት በዓለም ውስጥ ያለው የሕይወት ዐይነት ሁሉ በብዙ ሚሊዮን ዓመታት ተገኘ። በዚህ ሂደት ውስጥም ሰው ራሱ ሊጠቀስ የሚገባው ዋና የሕይወት ክፍል ነው። ሰው በእግዚአብሔር ካላመነ ይህን ወይም ይህን የመሰለ መላምት መፍጠር አለበት፤ ሲፈጥርም አሳቡ አመክንዮታዊ መሆኑን እንዴት ማወቅ እንደሚችል ብዙዎችን ያስገርማል።

አዝጋሚ ለውጥ ሁለት ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል። አንደኛው :- በአንድ ወገን ውስጥ ለምሳሌ በሰው ዘር ውስጥ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሰዎች ይረዝማሉ፤ ያጥራሉ፤ ይወፍራሉ፤ ይከሳሉ፤ መልካቸው ይለወጣል ... ወዘተ። ስለዚህ ዐይነት ለውጥ የሚነሣ ክርክር አይኖርም። ሁለተኛው፥ የሕይወት ሁሉ ውስብስብነት እያደገና እየተሻሻለ ወደሚገኝበት ሁኔታ መሄዱ ነው፤ ብዙ ጊዜ አዝጋሚ ለውጥ ሲባል ይህን ያመለክታል።

አንዳንድ ክርስቲያኖች የአዝጋሚ ለውጥን መላምት መቀበላቸውንና አስተሳሰባቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የሚወሰን መሆኑን በምዕራፍ 8 ሠ2 በዐጭሩ አትተናል። ስለዚህ ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ እዚህ ላይ በይበልጥ ማሰብ አስፈላጊ ነው።

1. የአምላካዊ አዝጋሚ ለውጥ መላምት (8)

እነዚህ ክርስቲያኖች በብዙ በኩል የዳርዊንን አስተሳሰብ ሲቀበሉ፥ እግዚአብሔር ዕቅዱ እንዲፈጸም በልዩ ልዩ ጊዜ በአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ውስጥ ገባና በመጨረሻ የተገኘው እንደ ፈቃዱ ሆነ። እግዚአብሔር በዚህ ሂደት ቢያንስ ቢያንስ የገባው፥ ሀ) በመጀመሪያው ቍሳዊ ዓለም መፈጠር፥ ለ) በመጀመሪያው ሕይወት ዐይነት መፈጠር፥ ሐ) በሰው መፈጠር ነው። ሌላው የአዝጋሚ ለውጥ ሂደትና ዕድገት ከራሱ ከተፈጥሮ የተገኘ ነው፤ ሆኖም በሳይንስ በኩል ዕድገቱ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ እንዴት እንደደረሰ ባይታይም፥ እግዚአብሔር በዕድገቱ ውስጥ ገብቶ መራው ማለት ይቻላል።

ይህን ዐይነት አስተሳሰብ ለመቀበል ግን ልዩ ልዩ ችግር ሊፈጠር እንደሚችል Grudem በተለይ ስድስት ምክንያቶችን በማቅረብ አሳይቷል :-

ሀ) የአዝጋሚ ለውጥ መላምት ዕድገቱ በ«አጋጣሚ» ይሄዳል እንጂ በዕቅድ የሚመራ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን «እግዚአብሔር ... አለ፤ ... እንዲሁም ሆነ» በማለቱ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ነገር እንደ ፈቃዱና እንደ ዕቅዱ ማድረጉ ይታያል፤ ዘፍ. 1፥3:6-7:9:11:14-15:24። «... ምድር ሕያዋን ፍጥረታትን እንደ ወገኑ፥ እንስሳትንና ተንቀሳቃሾችን የምድር አራዊትንም እንደ ወገኑ ታውጣ ...» ሲል እግዚአብሔር እያንዳንዱን ወገን አስቦ እንዲፈጠር አደረገ እንጂ በ«አጋጣሚ» የሆነ አይመስልም፤ ዘፍ. 1፥24። የኦሪት ዘፍጥረት አቀራረብ የሚያሳየው በፍጥረት ሥራ ውስጥ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ነገር መቈጣጠሩንና ማድረጉን እንጂ ለ«አጋጣሚ» ስፍራ መተዉን አይደለም።

ለ) መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሲናገር፥ ትእዛዙ ወዲያው መፈጸሙን ያሳያል፤ የአዝጋሚ ለውጥ አስተሳሰብ ግን ከብዙ ሙከራዎችና ለውጦች በኋላ ነገሮች እንደሚሆኑ ያስተምራል፤ መዝ. 33፥6:9።

ሐ) በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ተክሎችንና እንስሳትን «እንደ ወገኑ» እንዲያፈሩና እንዲበዙ ሲያዛቸው፥ አሳቡ በየወገኑ ልዩ ልዩ ቁመት፥ ቀለም፥ ችሎታ ... ወዘተ ቢገኝም፥ በየትውልዱ ሲያልፉ የተወሰነ ለውጥ የነበረ ይመስላል፤ ዘፍ. 1፥11-24።

መ) እንደ አዝጋሚ ለውጥ መላምት አሳብ ሰዎች ዛሬ ሲወለዱ ያለ እግዚአብሔር ሥራ እንደሚገኙ ይታሰባል። ዳዊት፥ «አቤቱ፥ አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና» ሲል፥ እግዚአብሔርም ለሙሴ «ለሰው አንደበቱን የሰጠው ማነው? ሰውን ደንቆሮ ወይም ዲዳ የሚያደርገው ማነው? ዐይን የሚሰጥ ወይም ዕውር የሚያደርገውስ ማነው? እኔ እግዚአብሔር አይደለሁምን?» በማለቱ የእግዚአብሔር ሥራ በእያንዳንዱ ሰው መገኘት ውስጥ ያለ ይመስላል፤ መዝ. 139፥13 አ.መ.ት.፤ ዘጸ. 4፥11 አ.መ.ት.። እንደዚሁም እግዚአብሔር ሣር እንዲያድግ ያደርጋል (መዝ. 104፥14፤ ማቴ. 6፥30)፤ ወፎችን (ማቴ. 6፥30) እና የዱር አራዊትን ይመግባል፤ መዝ. 104፥21:27-30። እግዚአብሔር በሕያው ነገር ሁሉ መኖር አሁን ቢሳተፍ፥ ህልውናው በ«አጋጣሚ» የሆነ ነው ብሎ ማሰብ አመክንዮታዊ አይመስልም።

ሠ) የአዳምና ከአዳም የሔዋን መፈጠር የአምላካዊ አዝጋሚ ለውጥን መላምት ያፈርሳል። ምክንያቱም እግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን መፈጠር ውስጥ ጣልቃ ከገባ፥ በሕያው ፍጥረት ታሪክ ሁሉ ለምን አልገባም? ለሚለው ጥያቄ መልስ ማግኘት እጅግ አስቸጋሪ ነው።

እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አገላለጥ በሥጋዊ በኩል ሰውን ከሚመስሉት ሌሎች ፍጡራን አዳምና ሔዋን እጅግ ሩቅ ነበሩ። አዳምና ሔዋን መነጋገር የሚችሉ፥ ግብረገባዊና መንፈሳዊ አሳብ የነበራቸው ፍጡራን ሲሆኑ፥ ከእግዚአብሔር ጋር አሳብ ለአሳብ መለዋወጥ እንኳ ይችሉ ነበር።

አንዳንዶች የኦሪት ጸሓፊ አዳምና ሔዋን ሲል፥ ስለ ሁለት ሰዎች ማለት ስለ አንድ ወንድና ስለ አንዲት ሴት የጻፈ አይመስላቸውም። ሆኖም የኦሪት ዘፍጥረት ታሪክ ከአዳምና ከሔዋን ወደ ሦስት ልጆቻቸው ታሪክና ከእነርሱ ቀጥሎ እስከ አብርሃም የትውልድ ሐረግ ድረስ ቀጥታ ይሄዳል። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ አዳም ሲናገር እንደ «አንድ ሰው» ይመለከተዋልና በእርሱ አማካይነት ኀጢአት ወደ ዓለም እንደገባ ሲያስተምር፥ የአዳምንና የክርስቶስን ሥራ ያነጻጽራል፤ ሮም 5፥12-21፤ 1ቆሮ. 15፥21-22:45-49። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች የአዳምንና የሔዋንን የልጆቻቸውንም ታሪኮች ሲጠቅሱ፥ እንደ ተራ ታሪኮች መቍጠራቸው ግልጥ

ነው፤ ለምሳሌ ማቴ. 23፥35፤ ሉቃ. 3፥38፤ ሐ.ሥ. 17፥26፤ 1ቆሮ. 11፥8-9፤ 2ቆሮ. 11፥3፤ ዕብ. 11፥4፤ 12፥24።

ረ) በሳይንስ በኩል በአዝጋሚ ለውጥ መላምት ብዙ ያልተፈቱ ችግሮች አሉና ከሳይንስ ምርምር የተነሣ ማንም ሰው ይህን መላምት እንዲቀበል የሚያደርግ አመክንዮታዊ ግዴታ አይኖርም። በዚህ ረገድ ያሉትን ችግሮች በሚከተለው ክፍል በዐጭሩ እናትታለን።

2. ከአዝጋሚ ለውጥ መላምት የተነሣ ያለው ትርምስ (9)

ዳርዊን የአዝጋሚ ለውጥን አሳብ በመጽሐፍ ጽፎ ካሳተመ በመቶ አርባ ዓመታት ውስጥ መላምቱ እውነተኛ መሆኑን ለማሳየት በሳይንስ በኩል ብዙ ሙከራ ተደርጓል። በብዙ ትምህርት ቤት መምህራን መላምትን እንደ ሐቅ ቈጥረው ያስተምሩታል፤ ሆኖም በቅርብ ጊዜ ልዩ ልዩ የሳይንስ ምሁራን መላምቱ መሠረት የሌለው ሆኖ እንዳገኙት በልዩ ልዩ መጻሕፍት ገልጠዋል። ከእነዚህ የሳይንስ ተመራማሪዎች መካከል አንዳንዶቹ በእግዚአብሔር የማያምኑ ናቸው። GRUDEM ከእነዚህ መጻሕፍት ልዩ ልዩ ሳይንሳዊ ምሳሌዎችን ያቀርባል። ከ140 ዓመታት በኋላ ብዙ ምርምርና ሙከራ ተደርጎ ገና ያልተረጋገጡ ነገሮች ብዙ ናቸው :-

ሀ) መላምቱ ትክክለኛ መሆኑን የሚያረጋግጥ አንድ እውነት (ክርክር የሌለበት ነገር) አልተገኘም።

ለ) አንድ አዲስ ወገን (እንስሳ፥ ተክል፥ ወፍ ... ወዘተ) በአዝጋሚ ለውጥ አልታየም።

ሐ) በሳይንሳዊ ሥራ ከአንድ ወገን አንድ አዲስ ወገን አልወጣም።

መ) በቅሪተ አካላት ምርምር ሁለት ተቀራራቢ ወገኖች ሲገኙ በሁለቱ መካከል የሽግግር መሰል ወገን አልተገኘም። በዚህም ፈንታ እንደ ሳይንስ ዘመን አቈጣጠር መሰል ወገኖች ድንገት ይገኛሉ፤ ድንገትም ይቀራሉ።

ሠ) ከቊሳዊ ነገሮች ሕያው ሴልን ማግኘት አልተቻለም።

3. የአዝጋሚ ለውጥ መላምት ውጤት (10)

መላምቱ ትክክለኛ ቢሆን ኖሮ ብዙ አስተያየት ማስከተል ይችል ነበር :-

ሀ) ሰው በ«አጋጣሚ» ከተፈጠረና ከእግዚአብሔር ካልተገኘ፥ በአምላክም ፊት ኀላፊነት ከሌለ፥ የሰው ሕይወት ዋጋ ምንድነው? ሰው ከቊሳዊ ነገሮች፥ ከጊዜና ከ«አጋጣሚ» ከሆነ፥ በታላቁ ዓለም ሲኖር ምንም ቁም ነገር የለውም። ይህ አስተሳሰብ ወደ ተስፋቢስነት ይመራል።

ለ) እግዚአብሔር ከሌለ ወይም እግዚአብሔር ለሰው ሕግን ካልሰጠ፥ ዳኛ የለም፤ ለግብረገብም መሠረት የለም፤ ይህ መልካም ነው ወይም ይህ ክፉ ነው ማለት አይችልምና።

ሐ) በአዝጋሚ ለውጥ የትምህርት መሠረት ሁሉ ወደተሻለ ሁኔታ ስለሚሄድ፥ ደካማ ሰዎችን ለመጠበቅና ለመርዳት ምክንያት የለም፤ እነርሱ ለወደፊት በሚገኘው ዓለም ስፍራ አይኖራቸውምና።

መ) ሁሉ ወደተሻለ ሁኔታ እየተለወጠ ከሄደ፥ የጥንት ዘመናት ጥበብ ዋጋቢስ ነው።

ሠ) መላምቱ ትክክለኛ ከሆነ፥ ሰው የላቀ እንስሳ እንጂ ልዩ ዐይነት ፍጡር አይደለም።

እነዚህን ነገሮች ስንረዳ፥ ልዩ ልዩ ፍልስፍና በተለይ ፋሺዝም፥ ኮሙኒዝምና ኍሳን የማጽዳት አመለካከት አሳባቸውን ለመደገፍ በአዝጋሚ ለውጥ መላምት ለምን እንደሚጠቀሙ ማስተዋል አያሰቸግርም።

ሠ) በፍጥረቱ የእግዚአብሔር ዓላማ

እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ ሰው ከተረዳ፥ ለምን ፈጠረው? የሚለው ጥያቄ ይነሣል። ሰዎች ለዚህ ጥያቄ መልስ ሲፈልጉ፥ አንዳንዶች፥ እግዚአብሔር እጅግ ሀብታም በመሆኑ ሁኔታውን መቈጣጠር ባለመቻሉ ውሃ ከምንጭ እንደሚፈስስ፥ ዓለም ከእርሱ ወጣ ይላሉ። ሌሎች ግን የዚህን አሳብ ተቃራኒ አስበው እግዚአብሔር በራሱ ድኻና ባዶ በመሆኑ ጐድለቱን ለመሙላት ዓለምን ፈጠረ ብለዋል። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር ዓለሙን እንዲፈጥር አስፈላጊ ነበረ። በእነዚህ አሳቦች መሠረት ዓለም ለእግዚአብሔር ይኖራል፤ ከመጠን በላይ እንዳያልፍም ሆነ እንዳያንስ ያደርጋል (11)።

ኢዮብ፥ «ሰው እግዚአብሔርን ሊጠቅም ይችላልን? ጠቢብ እንኳ ቢሆን ምን ይጠቅመዋል? አንተ ጻድቅ ብትሆን ሁሉን የሚችለውን አምላክ ምን ደስ ታሰኘዋለህ?» ብሎ ወዳጆቹን በመጠየቁ ሰው ለእግዚአብሔር አስፈላጊ አለመሆኑን አሳየ፤ ኢዮብ 22፥2-3 አ.መ.ት.። እንደዚሁም ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «አንዳችም እንደሚጐድለው በሰው እጅ አይገለገልም» ብሏል፤ ሐ.ሥ. 17፥25። እንደዚህ ከሆነ እግዚአብሔር ዓለምን ለምን ፈጠረ? የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ለክብሩ ሲል ፈጠረው የሚል ነው። በኢሳይያስ አፍ፥ ልጆቹን «ለክብሬ የፈጠርሁት» ብሎ ጠራቸው፤ ኢሳ. 43፥6-7። ዳዊትም፥ «ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ» ብሎ መስክሯል፤ መዝ. 19፥1።

ሰው ለራሱ ክብር ቢፈልግ ተገቢ አለመሆኑን እናውቃለን። እግዚአብሔር ግን ለራሱ ክብር ሲፈልግ ትክክለኛ ነው፤ ምክንያቱም ለእርሱ ክብር ይገባዋል። እግዚአብሔር የራሱን ክብር ባይፈልግ ኖሮ፥ ሰው የተፈጠረውን በማክበር ጣዖት አምላኪ ይሆን ነበር! በሰዎች መካከል እንኳ አንድ ስፖርተኛ ትልቅ ነገር ቢያደርግ፥ እስከንደክም ድረስ እናጨበጭብለታለን። ይህንም ማድረግ ደስ ይለናል። እግዚአብሔርን ስለ ታላላቅ ሥራዎቹ ስናከብረውማ እንዴት የበለጠ አንደሰትም! በዚህ ምክንያት 24ቱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ተወካይ ሽማግሌዎች፥ «ጌታችንና አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሁሉን ፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል» እያሉ ያመሰግኑታል፤ ይህን በማድረጋቸውም እጅግ ይደሰታሉ፤ ራእ. 4፥11።

ሰዎችና መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ ብቻቸውን አይደሉም። ሰው ሲያመልክ ከፍጥረት ሁሉ ጋር ያመልካል። በመዝሙር 148 ሰዎች ከመጠቀሳቸው በፊት መላእክት፥ ፀሐይ፥ ጨረቃ፥ ከዋክብት፥ ብርሃን ሁሉ፥ ሰማየ ሰማያት፥ የሰማያት በላይ ውሃ፥ አበቦች፥ ጥልቆች ሁሉ፥ እሳት፥ በረዶ፥ ዐመዳይ፥ ውርጭ፥ ዐውሎ ነፋስ፥ ተራሮች፥ ኰረብቶች፥ ዛፎች፥ አራዊት፥ እንስሳት፥ ተንቀሳቃሾችና ወፎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑት ታዝዘዋል። እነዚህ ፍጥረታት ከታዘዙ በኋላ ሰዎች በየደረጃው በተለይ ነገሥታት፥ አሕዛብ፥ አለቆች፥ ፈራጆች፥ ጐልማሶች፥ ቈነጃጅቶች፥ ሽማግሌዎችና ልጆች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ ታዝዘዋል። ሕይወት የሌለው ነገር እንዴት ያመሰግነዋል? ተብሎ ቢጠየቅም፥ መልሱ እያንዳንዱ ፍጥረት በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ያንጸባርቃልና ለእርሱ ክብር ይሰጣል። እግዚአብሔር ሁሉን ለዚህ ግብ ፈጠረ። ስለዚህ ከፍጥረት ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን በማመስገን ክብር እንሰጣለን። ከዚህ አሳብ ጋር፥ «በሰማያትና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ መላስም ሁሉ

ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ ይመሰክር ዘንድ ነው» እና «በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ :- በረከትና ክብር ምስጋናም ኀይልም ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ» የሚሉት ጥቅሶች ይስማማሉ፤ ፊል. 2፥10፤ ራእ. 5፥13። እንግዲህ ይህ የፍጥረት ዋጋ ነው፤ የፍጥረትም ግብ ነውና ፍጥረትን እንዴት ልንጠቀምበትና ልንጠብቀው እንደሚያስፈልግ ማሰብ ይገባናል።

## ማስታወሻ

(1) በዚህ ምዕራፍ ስለሚመረመሩ ነጥቦች ክርስቲያን ሊቃውንትም ሆኑ የሳይንስ ምሁራን ብዙ አሳብ ይኖራቸዋል። በዚህ ምዕራፍ ላይ ዋና ዋና አሳብ ለማቅረብ ስንፈልግ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን የሚቀበሉት ምእመናን ወደ ልዩ ልዩ አሳብ መድረስ እንደሚችሉ ለማሳየት ሞክረናል። ስለ አንዳንድ ነገሮች ግን ክርስቲያን ልዩ ልዩ መላምቶችን መቀበል እንደማይችል በግልጽ አሳይተናል። በአንዳንድ ነገር ላይ ያለን አሳብ ወደ አንድ መፍትሔ ሲያዘነብል ይታያል፤ ሆኖም ይህ እውነት ነው ለማለት አንደፍርም። አንባቢ ለራሱ ነገሩን ይመርምር፤ ከተቻለ ወደ አንድ አሳብ ይድረስ፤ እዚያም ከደረሰ በኋላ ከማይስማሙት በላይ ሆኖ አይፍረድ! ይህን ምዕራፍ ስናዘጋጅ በተለይ ሦስት መጻሕፍት ረድተውናል :-

GRUDEM ገጽ 262-310 ሰፊና ግልጽ አቀራረብ ነው።

MACLEOD, DONALD, በA FAITH TO LIVE BY ገጽ 52-65 በዐጭር አቀራረብ ለክርስቲያን ዋና ዋና ነገሮችን በጥሩ አኳኋን ያብራራል።

WENHAM, Dr GORDON, በWORD BIBLICAL COMMENTARY GENESIS 1-15 ገጽ 5-40 የኦሪት ዘፍጥረትን ምዕራፍ 1፥1-2፥3 የዕብራይስጥን አቀራረብ፥ ትርጉም፥ የቃላትን አሳብ፥ የጸሐፊውን ዓላማ በሰፊው ያብራራል።

(2) እነዚህ ነጥቦች NO FINAL CONFLICT ከፍራንሲስ ሼፈር መጽሐፍ ተጠቅሰው ከGRUDEM ገጽ 274 የተገኙ ናቸው።

(3) ዓለም በስድስት ሃያ አራት ሰዓት ቀኖች መፈጠሩን የሚያምኑ ብዙ ጊዜ በእንግሊዝኛ CREATIONISTS ይባላሉ።

(4) ይህን አሳብ የሚያቀርቡት በCREATIONISTS ውስጥ ከሚገኘው አንድ ክፍል ነው፤ ዋና መጽሐፋቸው በ HENRY M.MORRIS እና በ JOHN C.WHITCOMB በ1961 የተጻፈው THE GENESIS FLOOD ነው።

(5) WENHAM GENESIS 1-15 በገጽ 5-40 ይህን በሰፊው ያሳያል።

(6) MACLEOD ገጽ 60፤ ይህም አስተሳሰብ በWENHAM መጽሐፍ ላይ የተመሠረተ ነው።

(7) «አሮጌ ምድር» እና «አዲስ ምድር» የተባሉት የፍጥረት መላምቶች በእንግሊዝኛ "OLD EARTH" እና "YOUNG EARTH" THEORIES OF CREATION ይባላሉ። GRUDEM ገጽ 298 እና 304።

(8) የአምላካዊ አዝጋሚ ለውጥ መላምት በእንግሊዝኛ "THEISTIC EVOLUTION" ይባላል። GRUDEM ገጽ 275-280።

(9) GRUDEM ገጽ 280-286 ይመ.

(10) GRUDEM ገጽ 286-287 ይመ.

(11) BAVINCK ገጽ 167-168።

# ምዕራፍ 32 - የፍጥረት አጠባበቅ

አራት ዘፍጥረት ምዕራፍ አንድን ስንመለከት፥ የጸሐፊው ሰባት ዋና ዋና አሳቦች በምዕራፍ 30ለ ተዘርዝረዋልና ስለ ፍጥረት እነዚህን መሠረት አድርገን መቀበል ትክክለኛ ክርስቲያናዊ እምነት በመሆኑ ላይ አተኵረናል። ይህን ምዕራፍ ከሳይንስ ምርምር ጋር ለማዛመድ ልዩ ልዩ ሙከራ ተደርጓል፤ ዋና ዋና አስተሳሰቦችን በምዕራፍ 31 አትተናል። ለወደፊት ሌላ ዐይነት መላምት ይበጅ ይሆናል። ክርስቲያኖች ልዩ ልዩ መላምቶችን መከተል ይችላሉ፤ በሕይወታቸውም ነገሩን በይበልጥ ሲመረምሩ መሠረታዊ እምነታቸውን ሳይለውጡ የማዛመድ ጥረት ሲያደርጉ ከአንድ መላምት ወደ ሌላ ሊሻገሩ ይችላሉ። እዚህ ላይ ሁለት ነገሮች አሉ፤ አንደኛው :- መሠረታዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምን እንደሆነ ለይቶና ወስኖ መቀበል፥ ሁለተኛው :- በመጽሐፍ ቅዱስና በሳይንስ መካከል ግጭት ባለበት ስፍራ የተሻለውን የማዛመድ መላምት መምረጥና የሚበልጠው እስኪገኝ ድረስ የሌሎችን አሳብ አክብሮ ያገኘውን በትሕትና በአመክንዮታዊ መንገድ መረዳት ነው። ብዙ ክርስቲያኖች ለመላምቶች ከመጠን በላይ ትኵረት በመስጠት ከፍጥረት ትምህርት መገኘት ያለበትን ቁም ነገር አጥተዋል። ይህ እንዳይደርስብን ፍጥረትን እንዴት መመልከትና በምን መንገድ ልንጠቀምበት እንደሚገባን፥ እንደዚሁም የፍጥረት ተስፋ ምን እንደሆነ በዚህ ምዕራፍ እንመረምራለን።

## ሀ) በፍጥረት ላይ ሊኖር የሚገባው አመለካከት

ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ የእግዚአብሔር ተከታይ ነው። ጸሐፊው የፍጥረትን ሥራ ሲገልጥ በአራት የዕብራይስጥ ቃላት ተጠቅሟልና ከእነርሱ ሰው በሥራው እግዚአብሔርን መከተል እንዴት እንደሚገባው መማር እንችላለን።

አንደኛው ቃል «ሠራ» በሚለው ግሥ ተተርጕሟል፤ ዘፍ. 1፥26 አ.መ.ት.። እንግዲህ ሰው ሠሪ መሆን አለበት። እዚህ ላይ አዲስ ነገርን መሥራት ያመለክታል። ብዙ ዐይነት «ሥራ» ደጋግሞ ሲሠራ ያሰለቻል። አዲስ ድርሰትን መጻፍ፥ አዲስ ቤትን፥ ጠረጴዛን፥ ወምበርን መሥራት፥ አዲስ ሥዕልን መሣል ... ወዘተ ግን አያሰለችም። ስለዚህ የፈጣሪያቸውን አርአያ እንዲከተሉ ሰዎች ከሕፃንነታቸው ጀምረው አዲስ ነገሮችን መሥራት እንዲችሉ ምቹ መንገድ እንዲኖራቸው ማድረግ የወላጆችና የበላዮቻቸው ኀላፊነት ነው።

ሁለተኛው ቃል «አበጀ» በሚለው ግሥ ተተርጕሟል፤ ዘፍ. 2፥7። ሸክላ ሠሪ ከጭቃ ዕቃን እንደሚያበጀው ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ሰውን ከምድር ዐፈር አበጀው። የዕብራይስጡ ግሥ እግዚአብሔር ምን እንደፈለገ ዐውቆ ውብ እንዲሆን የሰውን አካል በብዙ ጥንቃቄ እንዳበጀ ያሳያል። ባበጀውም አካል ላይ የሕይወት እስትንፋስን እፍ አለበት። ሰዎች በኪነ ጥበብ ሥራዎቻቸው ላይ ውብና «ሕያው» ነገሮችን በማበጀታቸው ፈጣሪያቸውን ይከተላሉ።

ሦስተኛው ቃል «አድርጎ ሠራ» ተብሎ ተተርጕሟል፤ ዘፍ. 2፥22። የዕብራይስጡ ግሥ «ነደፈ» እና «ዐቀደ» የሚሉትን አሳቦች አጠቃልሎ ይይዛል፤ ሔዋን፥ አዳም የተመኘት፥ የተመቸችውና ለእርሱ አስፈላጊ ነበረችና፤ ሰውም

እንደዚሁ ለሕይወቱ፥ ለአካባቢውና ለሌሎች ሰዎች አስፈላጊው አድርጎ በመሥራት ፈጣሪውን ይከተላል።

አራተኛው ቃል «ፈጠረ» የሚለውን ግሥ ይተረጕማል፤ ዘፍ. 1፥1:21:27። ጸሐፊዎች በዚህ ግሥ ሲጠቀሙ ባለቤቱ እግዚአብሔር ብቻ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ ከምንም ወይም ከማይሆነው የሚሆነውን ይፈጥራል። ሰው ይህን ማድረግ አይችልም። እውነት ነው፥ እግዚአብሔር ሲፈጥር አስቀድሞ በፈጠረው ነገር ሊጠቀም ይችላል (ዘፍ. 1፥27ን ከ2፥7 ጋር ያስተያዩት)፤ ሆኖም ሰው በቍሳዊ ነገሮች እንደሚወሰን እግዚአብሔር አይወሰንም።

እንግዲህ እነዚህ አራት ቃላት ሰው በእግዚአብሔር መልክ በመፈጠሩ እግዚአብሔርን በፍጥረት ሥራ በመጠኑ ሊከተለው መቻሉን ያሳያሉ (1)።

አራቱ ቃላት እግዚአብሔር በምን ዐይነት ጥንቃቄና ዓላማ ምድርን እንደፈጠራት በማሳየታቸው «ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት» የሚለውን የዳዊትን ቃል ያብራራሉ፤ መዝ. 24፥1። ምድርም ስለፈጠራት ብቻ ሳይሆን (ኢዮብ 38፥4፤ መዝ. 19፥1)፥ ፍጥረቱን በመመገቡ (ማቴ. 6፥26፤ ቆላ. 1፥17)፥ ጸጋውን በፍጥረት ላይ በመግለጡ (ዘፍ. 9፥12-17፤ ማቴ. 5፥45)፥ ፍርዱን በፍጥረት ላይ በማሳየቱ (ዘፍ. 6፥7፤ መዝ. 104፥29) እና በዘመን ፍጻሜ በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል በመወሰኑ (ኤፌ. 1፥10፤ ቆላ. 1፥19-20) የራሱ መሆኗን አረጋግጧል።

እግዚአብሔር ምድሩን እንዲገዛ ለሰው ኀላፊነት ሰጥቷል፤ ዘፍ. 1፥28። ሰው ይህን ትእዛዝ ሲፈጽም፥ በምድር ላይ እንደ ተቈጣጣሪ (መዝ. 8፥6-8)፥ አትክልተኛ (ዘፍ. 2፥15) ወይም መጋቢ (ዘሌ. 25፥3-5፤ ማቴ. 25፥14-30) እንጂ እንደ ምድር ጌታና ባለቤት መሆን የለበትም። ሰው ለሚያደርገው ሁሉ በኀላፊነት ይጠየቃልና።

## ለ) የፍጥረት አጠቃቀም

ሰው ሲፈጠር ዘር የሚሰጡት ተክሎችና የዛፍ ፍሬዎች በምግብነት ተሰጡት፤ ዘፍ. 1፥29። ከውድቀቱ በኋላም ሕይወት ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ በምግብነት ተሰጠው፤ ሆኖም የእንስሳን ደም ከሥጋው ጋር እንዳይበላ ተከለከለ፤ ዘፍ. 9፥3-4። እንደዚሁም ለሥራው በጕልበታቸው የቤት እንስሳትን እንዲጠቀምባቸው ተፈቀደለት፤ ዘጸ. 20፥10:17።

ሰው በኀጢአት በመውደቁ ምድር እንደ ቀድሞው በረከት ላትሆንለት ትችላለች፤ ለምሳሌ ምድሩ እሾህንና አሜኬላን ታበቅልበታለች (ዘፍ. 3፥18)፤ ሰው በውሃና በእሳት ሊጐዳ (መዝ. 66፥12)፥ እንስሳት በሰዎች ላይ ሊነሡ (1ነገ. 13፥24) እና በሽታም ሰውን ሊያመነምንና ሊገድል ይችላል፤ ዘዳ. 28፥59። በሰውና በፍጥረት መካከል ያለው ግንኙነት ቢለወጥም፥ ከፍጥረት ሁሉ ጋር ሰው በቃል ኪዳን ውስጥ የሚገኝ ነውና በፍጥረት ላይ እንዲሠለጥን እንደ ቀድሞው ታዝዟል፤ ዘፍ. 9፥1-3:12-13።

ሰው ምድርን ሲገዛና ሲጠቀምባት፥ ዋናው ዓላማ ምቾት፥ ርካታና ሀብት እንዲያገኝባት ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ክብር እንዲታይባት ነው። በዚህ ምክንያት እግዚአብሔር የፈጠረውን መብል ከምስጋና ጋር መቀበል ይኖርብናል፤ 1ጢሞ. 4፥3።

ሰው በፍጥረት ሲጠቀም አንዳንድ ትእዛዛትን ማክበር ይኖርበታል ፦

1. የዕረፍትን ሰንበት ማክበር፤ ይህም ለሰው፥ ለእንስሳትና ለመሬት መሠረታዊ ሕግ በመሆኑ በትክክል ባይከበር ሰው፥ እንስሳ ወይም መሬት ይጐዳል፤ ዘጸ. 20፥10፤ ዘዳ. 5፥14፤ ዘሌ. 25፥2-6።

2. የተፈጠረውን ነገር አለማምለክ፤ ዘጸ. 20፥2-4፤ ሮም 1፥25።

3. ጐጂ የሆኑትን የፍጥረት ወገኖች ካልሆነ በስተቀር ሌሎችን አለማጥፋት፤ እያንዳንዱ የፍጥረት ወገን በእግዚአብሔር ለክብሩ ተፈጥሯልና ለወደፊት በሕይወት እንዲገኝ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ምክንያት «... እናቲቱን ከጫጩቶቿ ጋር አትውሰድ። እናቲቱን ስደድ፤ ጫጩቶችንም ለአንተ ውሰድ» ተብሎ ተጽፏል፤ ዘዳ. 22፥6።

ሰው ባለማሰቡ በማይገባ መንገድ በፍጥረት ሊጠቀም ይችላል። ለምሳሌ በቅርብ የሚገኙት የሚበላ ፍሬ የሚሰጡ ዛፎች ለጦር መሣሪያ ተብለው ሊቈረጡ ይችላሉ፤ ዘዳ. 20፥19-20።

በዚህ ርእስ በተለይ በዚህ ጉዳይ ላይ አንድ ችግር ሊነሣ ይችላል። አንዳንድ እንስሳትና ተክሎች ወፎችም ለሰው ጠቃሚዎች ናቸውና እነርሱ እንዲጠበቁ በቀላሉ ማሰብ ይቻላል። ሌሎች ግን ጠቃሚዎች ወይም ጐጂዎች አይደሉም። ለምሳሌ እግዚአብሔር የሜዳ አህያን፥ ጐሽን፥ ጉማሬን፥ ሌዋታንን (ዐዞ) ፈጠራቸው። ኢዮብ ከእነርሱ የእግዚአብሔርን ታላቅነት መረዳት፥ ደግሞም ፍጥረት ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር መፈጠሩን መገንዘብ ነበረበት፤ ኢዮብ ም. 39-41። እንግዲህ አራዊት ሰውን ሳይጐዱ በምድር እንዲኖሩ ማድረግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

እውነት ነው፤ ልዩ ልዩ እንስሳትና በራሪዎች፥ ለምሳሌ እንደ አይጥና እንደ የወባ ትንኝ ለሰው ሕይወት አደገኛ ናቸውና እነርሱን ማጥፋት ለሰው ኑሮና ጤና አስፈላጊ ይሆናል። ዕንቅፋቶች ሆነው የተገኙት ግን ከሰው ውድቀት የተነሣ ይመስላል። ሰው ዓለምን እንዲገዛ ስለታዘዘና ለእርሱ ዕንቅፋት በመሆናቸው ሊያጠፋቸው ከቻለ ይፈቀድለታል።

4. እያንዳንዱን ፍጡር እንደ ተፈጥሮው መጠቀም፤ ከዚህ ሐቅ ጋር ልዩ ልዩ የተያያዙ ትእዛዛት አሉ፤ ለምሳሌ «በበሬና በአህያ በአንድነት አትረስ» በማለቱ ተፈጥሮአቸው የተለያየ በመሆኑ በአንድነት ማገልገል አይመቻቸውም፤ ዘዳ. 22፥10። እንደዚሁም በሬው እህል ሲያበራይ አፉን ማሰር ኢተፈጥሮአዊ ድርጊት በመሆኑ ተከልክሏል፤ ዘዳ. 25፥4። መከልከሉ በሰው ላይ የሚደረገው ኢሰባዊ ድርጊት እንዳይፈጸም የሚያሳስብ ምሳሌ ነው፤ 1ቆሮ. 9፥9-10፤ 1ጢሞ. 5፥18።

ብሉይና አዲስ ኪዳናት በተጻፉባቸው ዘመናት ብዙ ሰው አልነበረምና አኗኗሩ በፍጥረት ላይ ያመጣው ለውጥ እጅግ አነስተኛ ነበር። አሁን ግን ሰው እየበዛ በመሄዱና በዘመናዊ ዘዴዎችና መሣሪያዎች በመጠቀሙ የዓለም ሁኔታ እየተለወጠና እየተጐዳ በመሄድ ላይ ይገኛል (2)። ሀብታም አገሮችና ሰዎች ከመጠን በላይ ከማትረፍ ቢቈጠቡና በመጠን ቢኖሩ ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔርን እያከበሩ እንደ ትእዛዛቱ ቢኖሩ፥ እግዚአብሔር ለሰው ያዘጋጀለት ይበቃው ነበር። ይህ ይሆን ዘንድ ግን የሰው አስተሳሰብ እንዲለወጥ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ የፍጥረት ጥበቃና እንክብካቤ እንዴት እንደሆነ ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል። ልዩ ልዩ የአውሬና የወፍ ወገኖች እንዳይጠፉ በቂ መናፈሻዎች አሉን? ዛፎች እንዳይጠፉ አንድ ሲቈረጥ ሌላ ይተከላልን? መሬት ፍሬያማ እንዲሆን የዕረፍት ሰንበት ይከበራልን? በኢትዮጵያ የዕርሻ፥ የጭነትና የቤት እንስሳት አጠቃቀም

ተፈጥሮአዊ ወይስ ኢተፈጥሮአዊ ነው? ለምሳሌ የላምን ፍግ ለማዳበሪያነት ከማዋል ይልቅ ለማገዶ መጠቀም፥ በአህያ ላይ የሚጫነውን ከመጠን በላይ ማድረግ፥ ውሻን ሁልጊዜ ጓሮ ማሰር፥ ዶሮን ዘቅዝቆ በእግሯ ማንጠልጠል ... ወዘተ ተገቢ ነውን? የሚሉትንና እነዚህን የሚመሳሰሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ክርስቲያናዊ ተግባር ነው።

## ሐ) የፍጥረት ተስፋ

አስቀድሞ እንደተጠቀሰው እያንዳንዱ ነገር ሲፈጠር መልካም ነበረና ሁሉ ከተፈጠረ በኋላ እጅግ መልካም ተብሏል። ከዚህም ጋር የተያያዘ ሌላ አሳብ ሊኖር ይችላል። ለምሳሌ ሕፃን ሲወለድ «መልካም ነው» ማለት ቢቻልም ገና «ፍጹም» አይደለም፤ ማደግ ያስፈልገዋልና። በዚህ ዐይነት አስተሳሰብ የተፈጠረው ሁሉ መልካምና ተስማሚ ቢሆንም፥ ገና ወደ ፍጹምነት አልደረሰምና ሰው ወደዚያ ደረጃ እንዲያደርሰው ተፈጥሯል፤ ይህንም በመሥራት ሰው ራሱ ወደ ፍጹምነት ይደርስ ነበር። እንግዲህ ሰው ሥራውን እንዲያውቅ እግዚአብሔር ገነትን ተከለለትና አትክልተኛነትን ከተማረና እንስሳትን ካስለመደ በኋላ ወደ ዓለም ሁሉ ሄዶ ፍጥረቱን ወደ ፍጹምነት ማድረስ ይችል ነበር፤ ዘፍ. 2፥8:15;19-20። በዚህ አሳብ መሠረት አንዳንድ ጊዜ ዛሬም እንኳ ይህን በመጠኑ ማድረግ ስለሚቻል፥ ሰው መሬት በይበልጥ ለምና ውብ እንዲሆንና እንስሳት ጠቃሚ እንዲሆኑ ፍጥረትን ወደ ፍጹምነት በመምራት ጥሪውን ይፈጽም ነበር። ሆኖም በጠቅላላ አስተያየት በኀጢአት ምክንያት ምድሪቱ የተረገመች ናት፤ ዘፍ. 3፥17። እንግዲህ ለፍጥረት ምን ተስፋ አለ? በተለይ ስለዚህ የሚናገረው የሮም መልእክት ምዕራፍ 8፥19-25 በመሆኑ፥ ከዚህ ክፍል ፍጥረትን በተመለከተ ዋና ዋና ነጥቦችን መዘርዘር ይረዳል። እዚህ ላይ ፍጥረቱ በሰውኛ አገላለጥ በነፍሰ ጡር ሴት ተመስሏል።

1. የአሁኑ የፍጥረት ሁኔታ፤ «ለከንቱነት ተገዝቷል»፤ «በጥፋት (በመበስበስ) ባርነት» በሚሉት ሐረጎች ተገልጧል። ወደዚህ ሁኔታ የደረሰው «በፈቃዱ አይደለም»፤ ሆኖም በሰው ውድቀት ምክንያት፥ ወይም ሰው ጥሪውን ባለመፈጸሙ፥ ወይም በሌላ ምክንያት መሆኑ አልተገለጠም፤ ቊ. 20-21።

2. የፍጥረት ናፍቆት፤ ከጥፋት ባርነት ነጻ ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነጻነት መድረስ ነውና በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃል። ናፍቆቱም በመቃተትና በምጥ ላይ በምትገኝ ሴት ተመስሏል፤ ቊ. 19-22።

3. የፍጥረት ናፍቆት ፍጻሜ፤ የፍጥረት ነጻነት ከእግዚአብሔር ልጆች ትድግና ጋር የተያያዘ ነው፤ ቊ. 23። በክርስቶስ ያመኑ በነፍሳቸው ድነዋል፤ ነገር ግን ሥጋቸው ከሞት በታች ነውና እስከ ትንሣኤ ዕለት በምልአት አይለወጡም፤ሙሉ በሙሉም አይድኑም፤ አዲሱን አካል አይቀበሉም፤ ልጅነታቸውም አይገለጥም፤ ቊ. 23፤ 1ቆሮ. 15፥42-44:51-52፤ 2ቆሮ. 5፥1-5፤ ይህን ትምህርት በ9ኛው ጥናት ላይ በስፋት እንደምንመለከተው ተስፋ እናደርጋለን። ፍጥረት ደግሞ ወደ ፍጹምነት የሚደርሰው የእግዚአብሔር ልጆች ወደ ፍጹምነት በሚደርሱበት በክርስቶስ ዳግም ምጽአት በትንሣኤው ዕለት ነው።

የፍጥረትን ፍጻሜ በተመለከተ ይህን አንቀጽ የሚያብራሩ ከአዲስ ኪዳን ሦስት ነገሮችን ማቅረብ እንችላለን ፡-

ሀ) ሐዋርያው ጴጥሮስ፥ «በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፤ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይቀልጣል (በእሳት ይጠፋል)፤ ምድርም በእርሷም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል ... የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል» በማለቱ

አሁን የምናውቀው ዓለም በዚህ ዘመን ፍጥረት እንደሚለወጥና ምንም ተስፋ እንዳናደርግ አሳይቶናል፤ 2ጴጥ. 3፥10-13። ሐዋርያው፥ በኖኅ ዘመን የነበረው ዓለም ሰጥሞ እንደጠፋ ሁሉ፥ የአሁኖቹ ሰማያትና ምድርም በእሳት እንደሚቀልጡ በእግዚአብሔር ቃል የተረጋገጠ እንደሆነ ተናግሯል፤ 2ጴጥ. 3፥7። አንዳንድ ሰዎች ዓለም ፈጽሞ በእሳት ይጠፋልና እግዚአብሔር አዲሱን ዓለም ይፈጥራል። ሌሎች ግን የአሁኑ ዓለም ይቃጠላልና እግዚአብሔር ከቀረው «ዐመድ» አዲስ ዓለምን ያበጃል። ያም ሆነ ይህ ለእኛ ለውጥ አያመጣም። ይህም ሲሆን የአሁኑ ዓለም «ፍፍቶት» ይፈጸማል። በአሁኑ ዓለም ያለው ሁሉ በምን ሁኔታ እንደሚገኝ ወይም እንደማይገኝ አልተገለጠም። ነቢዩ ኢሳይያስ፥ «አንበሳ እንደ በሬ ገለባ ይበላል ...» ሲል (ኢሳ. 65፥25) የሚመጣውን የሰላም ሁኔታ ለማመልከት እንጂ አሳቡን ቀጥታ እንደተጻፈው መተርጐም የጸሐፊው አሳብ አይመስልም።

ለ) እግዚአብሔር አዲስን ዓለም ሲፈጥር፥ ጽድቅ የሚኖርበት አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይገኛል፤ 2ጴጥ. 3፥13። ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ አዲሱ ዓለም እንደሚከተለው ጻፈ ፦ «አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፤ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛዪቱ ምድር ዐልፈዋልና ...። ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ»፤ ራእ. 21፥1-2።

የአሁኑ ዓለም መጨረሻ እንደዚህ ከሆነ፥ የአሁኑን ፍጥረት መጠበቅ ምን ጥቅም አለው? የሚሉ ሰዎች ቢኖሩ፥ እግዚአብሔር አብ ፈጠረው፤ እግዚአብሔር ወልድ ይደግፈዋል፤ መንፈስ ቅዱስ ይረብበታል፤ የአምላካችን ክብር ይታይበታል፤ እኛ እንጠቀምበታለን፤ የሚመጣውም ዓለም ጥላ ነው ብለን ልንመልስላቸው እንችላለን።

ሐ) ፍጥረት ሁሉ በእግዚአብሔር ዕቅድ ውስጥ ትልቅ ስፍራ አለው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኛችን ብቻ ሳይሆን የዓለም ፈጣሪና ደጋፊም ነው። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ዋናው የክርስቶስ ሥራ ሰውን ማዳኑ ቢሆንም፥ የእግዚአብሔር ዓላማ «በእርሱም በኩል ... በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ» ነው፤ ቆላ. 1፥19-20። ይህም በክርስቶስ አማካይነት መፈጸም ብቻ ሳይሆን «በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው»፤ ኤፌ. 1፥10። እግዚአብሔር ከፍጥረትም አለመጣጣምን አስወግዶ ሁሉ በስምምነት እንዲኖር ያደርጋል፤ ይህም በክርስቶስ የሚፈጸም ነው። በዚህም አዲስ ፍጥረት ውስጥ ዋናው ፍጡር ሰው ነው።

አንዳንድ ሰዎች ፍጥረት ከባርነት ወደ ነጻነት ስለሚሸጋገር፥ ክርስቶስ በደሙ ፍጥረትን እንደዋጀ ያስተምራሉ። ሆኖም ይህ ቤዛነትን አስመልክቶ ትክክለኛ አነጋገር አይመስልም። በመጀመሪያ፥ በሮም ምዕራፍ 8፥20-21 ስለ ቤዛነት የተገለጠው ሰውኛ ምሳሌያዊ አነጋገር ነው፤ ሁለተኛ፥ ክርስቶስ ቤዛ የሰጠው በሰው ኀጢአት ምክንያት ነው (ኤፌ. 1፥7)፤ ሦስተኛ፥ በክርስቶስ ቤዛነት የተነሣ ነጻነት የሚያገኙት የሚያምኑት ብቻ ናቸው፤ ሮም 3፥24-25። ሰው እንጂ ሌላው ፍጥረት ግብረገባዊ ባለመሆኑ ኀጢአት አያደርግም፤ አያምንምም። ክርስቶስ በመስቀሉ ደም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ሰላምን አደረገ፤ ከዚህም የተነሣ በምድርና በሰማይ ያለው ሁሉ ታርቆ በክርስቶስ ሙላት ይጠቃለላል፤ በሰላምም አብሮ ይኖራል፤ ቆላ. 1፥19-20።

ማስታወሻ

(1) DONALD MACLEOD በA FAITH TO LIVE BY ገጽ 52-54 ይመ.

(2) በTHE CARE OF CREATION በ2000 ዓ.ም. በIVP የታተመውን ገጽ 61-62 ይመ.

# ክፍል 2 - ሰማያውያን ፍጡራን

## ምዕራፍ 33 - መላእክት (1)

ሃይማኖቶች ሁሉ መንፈሳዊ ዓለም እንዳለ ይገልጣሉ፤ እንደየሃይማኖቱ ሁኔታ በመንፈሳዊው ዓለም ልዩ ልዩ ዐይነት መናፍስት እንዳሉ ይታሰባል። የፋርስ ሕዝብ በተለይ ስለ መላእክት ሰፋ ያለ ትምህርት ነበራቸው፤ ሆኖም አሳባቸው በመጀመሪያ ከአይሁድ የተገኘ ሳይሆን አልቀረም። አይሁድና ክርስቲያኖች ከጥንት ጀምሮ በመላእክት ያምኑ ነበር፤ ነገር ግን በአይሁድ መካከል ሰዱቃውያን (ሐ.ሥ. 23፥8) እና በክርስቲያኖች መካከል ብዙ ሊበራሎች በመላእክት አላመኑም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ይተርካል እንጂ መቼ እንደተፈጠሩ አይናገርም። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መላእክት ቍሳዊ አካል ሳይኖራቸው፥ አመክንዮታውያንና ግብረገባውያን፥ መንፈሳውያን ፍጡራን ናቸው። ብሉይ ኪዳን 100 ጊዜ፥ አዲስ ኪዳንም 200 ጊዜ ያህል ስለ መላእክት ይጠቅሳሉ፤ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት የሚሰጠው ትምህርት ሰፊ ነው፤ ይህንን ትምህርት በሚከተሉት አርእስት አጠቃልለን ለማየት እንሞክራለን።

### ሀ) አፈጣጠራቸውና ሁኔታቸው

#### 1. አፈጣጠራቸው

ዳዊት፥ «መላእክቱ ሁሉ አመስግኑት፤ ሠራዊቱ ሁሉ አመስግኑት ... እርሱም አዝዞአልና፥ ተፈጠሩም» እና ዕዝራ፥ «... ሰማዩንና የሰማያት ሰማይን ሠራዊታቸውንም ሁሉ ... ፈጥረሃል» በማለታቸው መላእክት እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ፥ በአጠገቡ የሚገኙ፥ በሰማያዊ ሁኔታ የሚኖሩ፥ እጅግ ብዙ መንፈሳውያን ፍጡራን መሆናቸውን እናስተውላለን፤ ነሀ. 9፥6፤ መዝ. 148፥2:5።

እግዚአብሔር ሁሉን ከፈጠረ በኋላ በሰባተኛው ቀን ስላረፈ፥ መላእክት ከዚህ ቀን በፊት እንደተፈጠሩ ግልጥ ነው፤ ዘፍ. 2፥1-2፤ ዘጸ. 20፥11። መላእክት ምን ጊዜ እንደተፈጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ ባይገልጥም፥ ብዙ ሊቃውንት በአንደኛው ቀን መሆኑን ያስባሉ፤ ለዚህም አንዳንድ ፍንጮች አሉ። ሙሴ :- «በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» ብሎ ወዲያውኑ «ምድር ...» ብሎ በመቀጠሉ የሰማይ ሁኔታና በእርሱ ያለው ሁሉ መደራጀቱን የሚያሳይ ይመስላል፤ ዘፍ. 1፥1-2። እንደዚሁም እግዚአብሔር የዓለምን መሠረቶች ሲተክል፥ መላእክት ሁሉ እልል እንዳሉ ስናነብ፥ መላእክት በመጀመሪያው ቀን መፈጠራቸውን ማሰብ ቀላል ነው፤ ኢዮብ 38፥5-6።

#### 2. ሁኔታቸው

ሰዎች በዚህ ሁኔታ ባለመኖራቸው ሁኔታቸውን ከሰው ሁኔታ ጋር ከማስተያየትና ከማነጻጸር በቀር ሌላ መንገድ አይገኝም።

ሀ) መናፍስት ናቸው፤ ዕብ. 1፥13:14። መሠረታዊ ሁኔታቸው ሲስተዋል፥ «ሥጋና ዐጥንት» የላቸውም (ሉቃ. 24፥39)፤ ሆኖም ከሰዎች ጋር እንዲነጋገሩ ለጊዜው የሰውን መልክ ሊይዙ ይችላሉ፤ ሰዎች ሲያዩአቸውም መላእክት መሆናቸውን ሊያስተውሉ ወይም ላያስተውሉ፥ «ሰዎች» ወይም «መላእክት» ተብለው ሊጠሩ

ይችላሉ፤ ዘፍ. 18፥2:22፤ 19፥1-2:5፤ ዳን. 9፥21፤ ማቴ. 28፥5፤ ሉቃ. 24፥4፤ ሐ.ሥ. 1፥10፤ 12፥7-11፤ ዕብ. 13፥2።

ሱራፌል ክንፎች ስላሏቸውና መላእክት «ስለሚበሩ» ሁሉም መላእክት ክንፍ እንዳላቸው በአንዳንዶች ይታሰባል፤ ሆኖም ብዙ ጊዜ «ሰዎች» ተብለው ስለሚጠሩ ለዚህ አሳብ መሠረት የለም፤ «በረረ» የሚለው ቃልም በአየር የሚሄዱትን እንጂ ክንፍ ያላቸውን አያሳይም። አንዳንዶች በስፍራ ውሱን መሆናቸውን ለመግለጥ አየራዊ ወይም እሳታዊ አካል እንዳላቸው አስተምረዋል፤ ሆኖም ለዚህ አሳብ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ ማግኘት ይከብዳል። ስዊድንቦርግ (SWEDENBORG)፥ መላእክት ሁሉ ሰዎች እንደነበሩ፥ በአካላዊ መልክ እንደሚኖሩና በመላእክት ዓለም ደረጃቸው በዚህ ዓለም በሚኖሩበት መሠረት መሆኑን አስተማረ (2)።

ለ) ከፍ ያለ የማሰብ ችሎታ አላቸው፤ ይህም ችሎታ ከዳንኤል፥ ከዘካርያስ፥ ከኢየሱስ እናት ከማርያም፥ ከሌሎችም ጋር ሲነጋገሩ ይታያል፤ ዳን. ም. 7-12፤ ሉቃ. 1፥11-20:28-37።

ሐ) ግብረገባውያን ናቸው፤ እንደ ፍጥረት ሁሉ መልካም ሆነው ተፈጠሩ (ዘፍ. 1፥31)፤ በኋላ ግን ብዙ መላእክት በኀጢአት ወደቁ (በሚከተለው ምዕራፍ ስለ ሰይጣንና ስለ መላእክቱ እናትታለን)። ያልወደቁ መላእክት የተመረጡ ናቸው፤ ጸጋ ተሰጣቸው፤ እስከ መጨረሻው ይታገሣሉና ቅዱሳን መላእክት ተብለዋል፤ ዘዳ. 33፥2፤ 1ጢሞ. 5፥21፤ ራእ. 14፥10።

መ) እጅግ ብዙና በቍጥር የማይደረስባቸው ናቸው፤ ዘዳ. 33፥2፤ መዝ. 68፥17፤ ማቴ. 26፥53፤ ዕብ. 12፥22፤ ራእ. 5፥11።

ሠ) ውሱን ናቸው፤ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ ሲገኝ፥ መላእክት በአንድ ቦታ ይገኛሉ፤ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ይሄዳሉ፤ ለመድረስም ጊዜ ሊጠይቃቸው ይችላል፤ ዳን. 10፥12-14፤ ሉቃ. 1፥26። ዕውቀታቸውም ውሱን ነው፤ ካልተገለጠላቸው በቀር የሚመጣውን አያውቁም፤ የሰውን አሳብ አያውቁም፤ ዳን. 2፥27-28፤ ማር. 13፥32።

ረ) ታላቅ ኀይል አላቸው፤ «ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኀያላን»፥ ተብለዋል፤ መዝ. 103፥20። በአንድ ሌሊት ብዙ ሰዎችን መግደል (2ነገ. 19፥35)፥ ታላቅ ድንጋይን ማንከባለል ችለዋል፤ ማቴ. 28፥2።

ሰ) ልዩ ልዩ ማዕረግ አላቸው፤ ለምሳሌ ሚካኤል «ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ» እና «የመላእክት አለቃ» ተብሏል፤ ዳን. 10፥13፤ ይሁዳ 9። ሌሎች የመላእክት አለቆች እንዳሉ አልተገለጠም።

ሸ) አያገቡም፤ በምድር ላይ ሰዎች እንደሚወልዱና እንደሚበዙ፥ እንደሚሞቱም አይደሉም፤ ማቴ. 22፥30፤ ሉቃ. 20፥34-36። አኗኗራቸው ከሰው አኗኗር እጅግ የተለየ በመሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ካልተገለጠ በስተቀር ልናውቀው አንችልም። ስለ ዘፍ. 6፥2-4 አተረጓጐም የሚከተለውን ምዕራፍ ይመ.

## ለ) ልዩ ልዩ መጠሪያዎቻቸውና ስሞቻቸው

መልአክ ማለት መልእክተኛ ወይም ወኪል ማለት ነው፤ የሚልካቸው እግዚአብሔር ነው።

1. መላእክት፥ የአምላክ ልጆች (ኢዮብ 1፥6፤ 2፥1)፥ ቅዱሳን (መዝ. 89፥5:7)፥ መናፍስት (ዕብ. 1፥14)፥ ጠባቂዎች (ዳን. 4፥13:17:23)፥ ዙፋናት፥

ኀይላት፥ ገዦችና ባለ ሥልጣናት ተብለው ይጠራሉ፤ ቆላ. 1፥16 አ.መ.ት.፤ ኤፌ. 1፥21።

2. ሚካኤል «የመላእክት አለቃ» በመሆኑ በመላእክት መካከል የተለያየ ደረጃ እንዳለ ግልጥ ነው (ሰ ይመ.)፤ ዳን. 10፥13: 21፤ ይሁዳ 9፤ ራእ. 12፥7። አንዳንድ ወገኖች ሚካኤል እግዚአብሔር ወልድ ነው ይላሉ፤ ሆኖም በይሁዳ 9 የሚገኘው ወቀሳ የፍጡር እንጂ የአምላክ አይደለም።

3. ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት የሚቆምና መልእክቶችን ለሰዎች የሚያቀርብ መልአክ ነው፤ ዳን. 8፥16፤ 9፥21፤ ሉቃ. 1፥11:19:26። በእግዚአብሔር ፊት ከሚቆሙት ሰባቱ መላእክት ውስጥ አንዱ ይሆናል፤ ራእ. 8፥2። ገብርኤል ያልተፈጠረ መንፈስ ነው ወይም ለመንፈስ ቅዱስም እንኳ የመጠሪያ ስም ነው ለሚሉ አንዳንድ ሰዎች ምክንያት የሚሆን አሳብ በእነዚህ ጥቅሶች ውስጥ አይገኝም።

4. በ2ኛ የቀኖና መጻሕፍት ከሚካኤልና ከገብርኤል ጋር ሩፋኤልና ፋኑኤል በመጽሐፈ ሄኖክ ምዕራፍ 10፥ ዑርኤል ደግሞ በመጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል ምዕራፍ 2 ተጠቅሰዋል። በመጽሐፈ ሄኖክ ም. 6፥1-7 ዑርኤል፥ ሩፋኤል፥ ራጉኤል፥ ሚካኤል፥ ሠረቃኤልና ገብርኤል ከነአገልግሎታቸው ተጠቅሰው ይታያሉ።

5. የእግዚአብሔር መልአክ፤ አንዳንድ ጊዜ እንደ ገብርኤል የተላከ መልአክ ሲሆን በሌላ ጊዜ እግዚአብሔር ራሱ ለጊዜው በሰው መልክ ሆኖ የሚገለጥበት ነው፤ ም. 2 ለ1 ይመ.። የእግዚአብሔር መልአክ አጋርን፥ «ዘርሽን እጅግ አበዛለሁ ...» ብሎ ተስፋ ሲሰጣት፥ «እርሷም ይናገራት የነበረውን የእግዚአብሔርን ስም ኤልሮኢ» ብላ በመጥራት እግዚአብሔርን ያየች መሆኗን መሰከረች፤ ዘፍ. 16፥7-14። የእግዚአብሔር መልአክ አብርሃምን :- «... አንድ ልጅህን ለእኔ አልከለከልህምና ...» በማለቱ እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን አሳየ፤ ዘፍ. 22፥11-12። እንደዚሁም ያዕቆብንም የእግዚአብሔር መልአክ :- «... ሐውልት የቀባህበት በዚያም ለእኔ ስእለት የተሳልህበት የቤቴል አምላክ እኔ ነኝ» ብሎ ተናገረው፤ ዘፍ. 31፥11-13። የእግዚአብሔር መልአክ ለሙሴ ሲታየውም :- «እኔ የአባትህ አምላክ፥ የአብርሃም አምላክ ... ነኝ» በማለቱ እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን አረጋገጠለት፤ ዘጸ. 3፥2:6። ለኢያሱ የታየው የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ከአነጋገሩና ከሰጠው ትእዛዝ አንጻር እግዚአብሔር ራሱ ይመስላል፤ ኢያሱ 5፥13-15። እነዚህን የሚመስሉ ታሪኮች በመሳ. 6፥12-14፤ 13፥21-22 ተጽፈው ይገኛሉ። ፕሮቴስታንቶች እግዚአብሔር ራሱን በዚህ ዐይነት ሲገልጥ፥ እግዚአብሔር ወልድ እንደሆነ ያስባሉ፤ ይህ ከትሥጉት ትምህርት ጋር ቢስማማም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ይህን አሳብ የሚያረጋግጥ አይገኝም። ይህ ዐይነት ክሥተት በእንግሊዝኛ ቋንቋ THEOPHANY (የእግዚአብሔር መታየት) ይባላል።

በሌሎች ጥቅሶች የእግዚአብሔር መልአክ ከእግዚአብሔር ከራሱ የተለየ መሆኑ ይታያል፤ ለምሳሌ እግዚአብሔር ለእግዚአብሔር መልአክ ትእዛዝ ሲሰጥ እናነባለን፤ 2ሳሙ. 24፥16፤ ዘካ. 1፥11-13።

ሐ) ሌሎች ሰማያውያን ፍጡራን

መላእክት ተብለው ያልተጠሩ ሦስት ሌሎች ሰማያውያን ፍጡራን አሉ። አንዳንዶች እነዚህን ፍጡራን እንደ መላእክት ይቈጥሯቸዋል፤ ሌሎች ደግሞ ለብቻቸው ነጥለው ይመለከቷቸዋል።

1. ሱራፌል፤ እግዚአብሔርን እያከበሩ ያመልኩታል፤ ከእነርሱም አንዱ ኢሳይያስን አገልግሏል፤ ኢሳ. 6፥2-7።

2. ሕያዋን ፍጡራን፤ እነዚህ ፍጡራን በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ ወይም ከዙፋኑ በታች ይገኛሉ፤ ሕዝ. 1፥5-14፤ ራእ. 4፥6-8። በሕዝ. 10፥15:20-22 ኪሩቤል ተብለዋል።

3. ኪሩቤል፤ ሁለት «ኪሩቦች» በታቦት ላይ ተሠሩ፤ እግዚአብሔር በኪሩቦች መካከል ሙሴን አነጋገረው፤ ዘጸ. 25፥18-22፤ ዘኁ. 7፥89። እግዚአብሔር በኪሩቤል ላይ መቀመጡ ብዙ ጊዜ ተጽፏል፤ 2ነገ. 19፥15፤ መዝ. 18፥10፤ ሕዝ. 10፥1-3። ኪሩቤል በመጋረጃ (ዘጸ. 36፥8:35)፥ በቤተ መቅደስ ላይ (2ዜ.መ. 3፥7-14) እና በራእይ በታየው ቤተ መቅደስ ተሠርተዋል፤ ሕዝ. 41፥18-25።

በታቦቱ ላይ፥ በመጋረጃውና በቤተ መቅደሱ የነበሩት ኪሩቤል ምስሎች ነበሩ። የምን ምስሎች ነበሩ? ለሚለው ጥያቄ ሁለት መልሶች ይቀርባሉ፤ አንደኛውና የተለመደው መልስ ሰማያውያን ፍጡራን ናቸው የሚለው ነው፤ ተግባራቸውም ገነትን መጠበቅ ነበር (ዘፍ. 3፥24)፤ በሕዝቅኤልና በዮሐንስ ራእይ ያሉ ኪሩቤል ሕያዋን ፍጡራን ናቸውና፤ ሕዝ. 10፥1-22፤ ራእ. 4፥6-8። አንዳንዶች ግን ኪሩቤል ለእግዚአብሔር መንግሥት የበቁ ሰዎች ምሳሌዎች ናቸው ይላሉ። በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ መሠረት በገነት ምሥራቅ የነበሩ የኪሩቤል ምስሎች መገኘት እነአዳም ወደ ገነት የማይገቡበትን ምክንያት ሲገልጥ፥ የከለከላቸው ግን የእግዚአብሔርን ኀይል የሚገልጠው የነበልባል ሰይፍ ነበር። በታቦቱ ላይ የነበሩ ኪሩቤል ፊቶቻቸውን ወደ ስርየት መክደኛው አዙረው የሚመለከቱት የሰው መዳን የሚገኝበትን ለማስታወስ ነው። ከሌሎች ይልቅ ለእግዚአብሔር ኪሩቤል ቅርብ የሆኑት ሰው በመልኩ በመፈጠሩ ነው፤ ሰውም ለወደፊት ከመላእክት በላይ ይሆናል፤ 1ቆሮ. 6፥3። ሌሎችም ደግሞ ኪሩቤል፥ ሰዎችንና ፍጥረትን ሁሉ ወክለው በእግዚአብሔር ዘንድ ይገኛሉ ይላሉ። ያም ሆነ ይህ ኪሩቤል በእግዚአብሔር ዘንድ የሚገኙ ፍጹማን ፍጡራን መሆናቸውና ዋና አገልግሎታቸውም እርሱን ማመስገን መሆኑ የትርጒማችን ዐቢይ አሳብ ነው።

መ) አገልግሎታቸው

1. አስቀድመን እንዳየነው ዋና አገልግሎታቸው እየተደሰቱ እግዚአብሔርን ማመስገን ነው፤ ዕብ. 12፥22፤ ራእ. 5፥11-12፤ 7፥11-12።

2. በሰማያዊ ሰፍራ ከወደቁት መላእክት ጋር ተዋግተው ማሸነፍ ነው፤ ዳን. 10፥13:21፤ ራእ. 12፥7-8፤ 20፥1-3።

3. የዓለምን ሁኔታ እየተመለከቱ በምድር ይመላለሳሉ፤ ዘካ. 1፥10-11 (ከኢዮብ 1፥6-10 እና ከ2፥1-5 ጋር ይመ.)።

4. ከዚህ በላይ እንዳየነው ከእግዚአብሔር ለአገልጋዮቹ መልእክቶችን ያቀርባሉ፤ ሐ.ሥ. 8፥26፤ 10፥3-8:22፤ 27፥23-24። የሙሴንም ሕግ በመስጠት ተሳትፈዋል፤ ዘዳ. 33፥2፤ ሐ.ሥ. 7፥52-53፤ ገላ. 3፥19፤ ዕብ. 2፥2።

5. ከእግዚአብሔር ፍርዶች የተወሰኑትን በሰው ላይ ያመጣሉ፤ ለምሳሌ ቸነፈርን በእስራኤል ላይ በማምጣት (2ሳሙ. 24፥15-17)፥ ከአሦር ጦር ሠራዊት ብዙ ታላላቅ ሰዎችን በመግደል (2ዜ.መ. 32፥21)፥ ለእግዚአብሔር ክብርን ባለመስጠቱ ንጉሥ

ሄሮድስን በትሎች ተበልቶ እንዲሞት በማድረግ (ሐ.ሥ. 12፥23)፥ የእግዚአብሔርን የቍጣ ጽዋዎች በምድር ውስጥ በማፍሰስ፤ ራእ. 16፥1።

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን በመጀመሪያው ምጽአቱ አገልግለውታል፤ በዳግም ምጽአቱም አጅበው ያገለግሉታል። በመጀመሪያ ሲመጣ በተለይ በልደቱ (ማቴ. 1፥20:24፤ 2፥13:19፤ ሉቃ. 1፥11-38፤ 2፥9-15፤ ዕብ. 1፥6)፥ ከተፈተነ በኋላ (ማቴ. 4፥11፤ ማር. 1፥13)፥ በጌቴሴማኒ (ሉቃ. 22፥43)፥ በትንሣኤውም (ማቴ. 28፥2-7፤ ማር. 16፥5-7፤ ሉቃ. 24፥4-7:23፤ ዮሐ. 20፥12-13፤ 1ጢሞ. 3፥16) አገለገሉት። በዳግም ምጽአቱ ጊዜ መላእክት ምጽአቱን ያውጃሉ (1ተሰ. 4፥16፤ ራእ. 18፥1-2:21፤ 19፥17-18 ... ወዘተ)፤ በክብር ያጅቡታል፤ የተመረጡትንም ይሰበስባሉ፤ ማቴ. 24፥31፤ 25፥31።

7. ሰዎችን፥ በተለይ የእግዚአብሔርን ሰዎች ይጠብቃሉ፤ መዝ. 34፥7፤ 91፥11-12። ለምሳሌ ሐዋርያትን ከእስር ቤት አወጡ፤ ሐ.ሥ. 5፥17-20፤ 12፥6-11።

መላእክት ሰዎችን እንደሚጠብቁ ግልጥ ነው፤ ሆኖም ለእያንዳንዱ ሰው ወይም አማኝ የግል ጠባቂ አለውን? የሚለው ጥያቄ ይነሣል። ክርስቶስ ስለ ሕፃናት፥ «... ተጠንቀቁ መላእክታቸው በሰማያት ዘወትር የአባቴን ፊት ያያሉ» ብሏል፤ ማቴ. 18፥10። በመዋዕለ ሕፃናት ተቀጥረው የሚሠሩ ሁሉ ሕፃናትን ሁሉ በአንድነት ሲጠብቁ፥ ለእያንዳንዱ ሕፃን የራሱ የግል ጠባቂ እንደማይገኝ ሁሉ፥ የክርስቶስም ቃል ለእያንዳንዱ ሕፃን አንድ መልአክ መኖሩን ላያሳይ እንደሚችል የሚተረጕሙ አሉ። ቃሉ ግን ሕፃናትን ክርስቶስ እንደሚወዳቸው፥ መላእክት እንደሚጠብቋቸውና የጌታን ፊት በማየታቸው ለተመደበላቸው ሥራ የበቁ መሆናቸውን ስለሚያረጋግጥ፥ ሰው ከሕፃናት ጋር የሚያደርገውን በጥንቃቄ ማድረግ አለበት። ጴጥሮስም ከእስር ቤት ወጥቶ በማርቆስ እናት ቤት በር ላይ ሲያንኳኳ ሮዴ ጴጥሮስ መሆኑን ለተሰበሰቡ ሰዎች ስትነግራቸው፥ አንዳንዶች «መልአኩ ነው» አሏት። አሳባቸው ምን እንደሆነ በትክክል ለማወቅ አንችልምና የእነዚህ ሰዎች ቃል ለእያንዳንዱ ክርስቲያን ጠባቂ መልአክ አለ ብሎ ለመናገር በቂ ምክንያት አይገኝበትም፤ ሐ.ሥ. 12፥12-15።

ሠ) ከምእመናን ጋር ያላቸው ግንኙነት

መላእክት፥ ሱራፌልና አራቱ ሕያዋን እንስሳት እግዚአብሔርን ያከብራሉ፤ መዝ. 103፥20፤ ኢሳ. 6፥2-3፤ ራእ. 4፥8። መላእክት በደኅንነት ሥራ ይደሰታሉ። ክርስቶስ ሲወለድ አመሰገኑ (ሉቃ. 2፥13-14)፤ ሰው ንስሓ ሲገባ ይደሰታሉ (ሉቃ. 15፥10)፤ በቤተ ክርስቲያን ስብሰባዎች ይገኛሉ። በዚህ ምክንያት ሐዋርያው ጳውሎስ፥ ሴቶች ከመላእክት የተነሣ ተገቢ የራስ መሸፈኛ መልበስ እንደነበረባቸው ጽፏል፤ 1ቆሮ. 11፥10። ሰዎች ከአይሁድና ከአሕዛብ ጋር በአንድነት ሲያመልኩ፥ «ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ ... በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ስፍራ ውስጥ ላሉት አለቆችና ሥልጣናት» ይታወቃል፤ ኤፌ. 3፥10። ጴጥሮስ፥ የእግዚአብሔር ዕቅድ በምእመናን ዘንድ እንዴት እንደሚፈጸም «መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ» ብሎ ጽፏል፤ 1ጴጥ. 1፥12። ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ዐደራ ሲሰጥ፥ «በእግዚአብሔርና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በተመረጡትም መላእክት ፊት እመክርሃለሁ» ብሏል፤ 1ጢሞ. 5፥21። ሐዋርያው የሚደርስበትን ሁሉ መላእክት እንደሚያዩ ያውቃል፤ 1ቆሮ. 4፥9።

ረ) ለመላእክት አገልግሎት የምእመናን አጸፋ

ከዚህ በላይ የተጻፈውን ትምህርት ሁሉ ስንመለከት፥ የመላእክት አገልግሎት መንፈሳዊ ዓለም እንዳለ ያሳስበናልና ስንጸልይ ወደዚያ ዓለም በእምነት እንገባለን፤ ዕብ. 12፥22-24። እኛም መላእክትን የምናይበት ችሎታ አልተሰጠንም፤ እንደሚያገለግሉን ግን በእምነት እናውቃለን፤ አንድ ነገር ተፈጽሞ ስናይ የመልአክ ሥራ ሳይሆን አይቀርም ብለን ልናስብ እንችላለን፤ እንደዚህ ካሰብን እግዚአብሔር በመልአኩ አማካይነት ስለፈጸመልን ልናመሰግነው ይገባናል፤ ዕብ. 1፥14። ብዙ ጊዜ ሰው እንደማያየን ስናውቅ፥ እግዚአብሔር፥ ክርስቶስ፥ መንፈስ ቅዱስና የተመረጡ መላእክት እንደሚያዩን ዐውቀን እንዳናሳዝናቸው መጠንቀቅ ይገባናል፤ 1ጢሞ. 5፥21።

የተመረጡ መላእክት እንዳሉ ስናስብ፥ የወደቁ መላእክት እንዳሉም እናውቃለን፤ ለእነርሱ የደኅንነት ተስፋ የለም (የሚከተለውን ምዕራፍ ይመ.)። ስለዚህ ለሰዎች የደኅንነት ተስፋ ስለተሰጠ የሰው ዕድል ከፍ ያለ ነው።

ለመላእክት ስለሚሰጠው የምእመናን አጸፋ ሦስት ጥያቄዎች ሊነሡ ይችላሉ ፦

1. ለመላእክት ልዩ አክብሮት መስጠት ተገቢ ነውን?

ዳዊት ስለ ሰው ሲጽፍ ፦ «ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምስጋና ከለልኸው» ብሎ የሰውንና የመልአክን የማዕረግ ግንኙነት ገለጠ፤ መዝ. 8፥5። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ይህን ጥቅስ አትቶ፥ «... ከመላእክት ጥቂት እንዲያንስ ተደርጎ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ የክብርና የምስጋና ዘውድ ተጭኖለት እናየዋለን» ብሎ ገልጦታል፤ ዕብ. 2፥6-9። እንግዲህ በዚህ ዓለም ሰው ከመላእክት ትንሽ ሲያንስ፥ በሚመጣው ዓለም በመጠኑ ብልጫ የሚኖረው ይመስላል፤ ሰው በመላእክት እንኳ ይፈርዳልና፤ 1ቆሮ. 6፥3። መላእክት ክብር አላቸው፤ ቅዱሳን ይባላሉ፤ ሆኖም በአዲስ ኪዳን አገላለጥ ምእመናን ሁሉ ቅዱሳን ተብለዋል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ሰዎች መላእክትን ሲያዩ ብዙ ጊዜ ድንጋጤ ወይም ፍርሀት ይይዛቸዋል። የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ራሱን ሲገልጥለት፥ ኢያሱ ወደ ምድር በግምባሩ ተደፍቶ ሰገደ፤ በኋላም የቆመበት መሬት የተቀደሰ መሆኑን ሲሰማ ጫማውን ከእግሩ አወለቀ፤ ኢያሱ 5፥13-15። ይህ ታሪክ፥ የሙሴን ታሪክ ለማስታወስ ይገፋፋልና ይህ «ሰው» እግዚአብሔር በሰው መልክ እንደተገለጠ ሊታሰብ ይችላል፤ ዘጸ. 3፥1-6። በለዓም የእግዚአብሔርን መልአክ ሲያይ ፈርቶ ሰገደ፤ በግምባሩም ወደቀ፤ ዘኍ. 22፥31። ነቢዩ ዳንኤልም መልአኩ ገብርኤልን ሲያይና ሲሰማ፥ ፈርቶና ደንግጦ በግምባሩ ተደፋ፤ ገብርኤል ግን ዳሰሰውና ቀጥ አድርጎ አቆመው፤ ዳን. 8፥15-18። ዘካርያስ ገብርኤልን ሲያይ፥ «ደነገጠ፤ ፍርሀትም ወደቀበት»፤ ድንግል ማርያምም ከመልአኩ ንግግር የተነሣ «ደነገጠች»፤ ገብርኤልም ሊያጽናናቸው ዘካርያስን «አትፍራ»፤ ማርያምንም «አትፍሪ» አላቸው፤ ሉቃ. 1፥12-13:28-30። ሐዋርያው ዮሐንስ ብዙ ነገሮችን ለገለጠለት መልአክ ሁለት ጊዜ ሲሰግድለት፥ «እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱስም ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ ...»፤ «እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ስገድ» አለው፤ ራእ. 19፥9-10፤ 22፥8-9። የመልአኩ ቃል የእግዚአብሔርን ቃል እንደሚጠብቁት ሁሉ ራሱ የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆነ፥ ለራሱ ልዩ አክብሮት እንዳልጠየቀና ስግደት

ለእግዚአብሔር የሚሰጥ መሆኑን በትኩረት ያሳያል። አንዳንዶች ለእግዚአብሔር በሚሰጠው የአምልኮ አገላለጥና ለሰው ወይም ለመላእክት በሚሰጠው የአክብሮት አገላለጥ መካከል ልዩነት ማድረግ ይወዳሉ (3)። ሆኖም መልአኩ ወይም ጴጥሮስ ስለዚህ ዐይነት ልዩነት አልተናገሩም፤ ከሰገዱላቸው ሰዎች ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና አንድነት በጉልሕ ገለጡ እንጂ አክብሮት መፈለጋቸውን የሚያሳይ አንድም ፍንጭ አልሰጡም፤ ሐ.ሥ. 10፥25-26። ሐዋርያው ጳውሎስም ፦ «ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ» ብሎ በማስጠንቀቁ፥ አንዳንድ ሰዎች በቀላሉ ለመላእክት በማይገባ መንገድ ክብር ሊሰጡ እንደሚችሉ አሳይቷል፤ ቆላ. 2፥18። ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው፥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለመላእክት ስግደት እንዲደረግ የሚያሳስብ አንድም ትእዛዝ አይገኝም።

2. መላእክት ለእኛ እንዲያማልዱ መጠየቅ ተገቢ ነውን?

መላእክት ከእግዚአብሔር ወደ ሰው ይላካሉ፤ ወደ እግዚአብሔር ይመለሳሉ፤ ዘፍ. 28፥12። ሲመለሱ የሚያገኙትን ሊናገሩ ይችላሉ (ኢዮብ 1፥6-10፤ 2፥1-5፤ ዘካ. 1፥12፤ ማቴ. 18፥10)፤ ከተመለከቱትም የተነሣ እንደሚለምኑ ወይም እንደሚያመሰግኑ ማሰብ አይከብድም። ሆኖም እንደዚህ እንደሚያደርጉ መጽሐፍ ቅዱስ ማረጋገጫ አይሰጥም። (በዘካ. 1፥12 የመልአኩ «... እስከ መቼ ነው?» የሚለው ሐረግ እንደ ዐውዱ ልመናን የሚያሳይ ሳይሆን ጥያቄን የሚያመለክት ይመስላል)። ሰዎች ከመላእክት ጋር ሲነጋገሩ፥ መላእክትን ብዙ ጥያቄዎች ቢጠይቋቸውም፥ ለእግዚአብሔር እንዲነግሩላቸው ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ አናገኝም።

መላእክትና ክርስቲያኖች በአንድነት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ቢሆኑምና መላእክት ቢያዩአቸውም፥ ለሰዎች ግን አይታዩም፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ካልተገለጠ በስተቀርም ስለ መላእክት ሁኔታ ሰዎች ምንም አያውቁም። ሰው መልአክን እንዲለምንለት ከመጠየቁ በፊት ለአንዳንድ ጥያቄዎች መልስ ማግኘት ይገባዋል። ለምሳሌ ፦ መላእክት ውሱን በመሆናቸው (እንደ እግዚአብሔር በሁሉ ዘንድ አይገኙም) አንድ መልአክ አንድን ሰው አይቶ እንደሚሰማው በምን ይታወቃል? መልአክ የሚሰማው ቢመስለውም የትኛው መልአክ እንደሆነ ለማወቅ ምን ማረጋገጫ አለ? የሚሰማው ቢመስለውም የትኛው መልአክ እንደሆነ ለማወቅ ምን ማረጋገጫ አለ? በስም የሚጠራው መልአክ ቢገኝም መልአኩንስ በስም መጥራት ምን መሠረት አለው? መልአኩ ቢገኝም ሌላ እንኳ በሌላ ስፍራ እንደማይገኝ ማሰብ ትክክለኛ ነውን? ልመና በእግዚአብሔር ቃል ምሳሌና ትእዛዝ አገልግሎት እንደሌለው በምን ያውቃል? መልአኩ ሰውዬው አንድ ነገር እንዲያደርግለት በዚህ ዐይነት የማያገኝ ከሆነ፥ የሚስማማበት ምን ምክንያት አለ? ... ወዘተ የሚሉ ናቸው።

3. መላእክትን ለማየት ተስፋ ማድረግ ተገቢ ነውን?

በአዲስ ኪዳን ዘመን ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ መላእክት ለፊልጶስ፥ ለቆርኔሌዎስ፥ ለጴጥሮስና ለጳውሎስ እንደታዩ እናነባለን፤ ሐ.ሥ. 8፥26፤ 10፥3-6፤ 12፥6-11፤ 27፥23-24። የዕብራውያን ጸሐፊ ከሐዋርያት በኋላ ለነበሩ ምእመናን ሲጽፍ (ዕብ. 2፥3)፥ ሳያስተውሉ መላእክትን መቀበል በመቻላቸው የእንግዳ ተቀባይነት መንፈስ እንዲያሳዩ አዘዛቸው፤ ዕብ. 13፥2። ስለዚህ መላእክት ሊታዩን ይችላሉ፤ ከእግዚአብሔር መልእክት ሊያመጡልን ወይም በሌላ መንገድ ሊያገለግሉን ይችላሉ። ሆኖም መናፍስት በመሆናቸው በሰው መልክ እንዲታዩ መጠበቅ የተለመደ አይደለም። ለሰው አንድ ነገር ቢታየው ብዙ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገዋል፥ «ሰይጣን ራሱ የብርሃንን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና»፤ 2ቆሮ. 11፥14። እግዚአብሔር

በቃሉ እውነትን ሰጥቷልና ይህን የሚቃረንና ተቃራኒውን የሚናገር ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ገላ. 1፥8። ስለዚህ መልአክን እንድናይ የሚያደፋፍር ትእዛዝ አናገኝም፤ ሆኖም የሚቻል መሆኑን ዐውቀን አንድ ክሥተት ቢታየን በጥንቃቄ ልንመረምረው ይገባናል።

## ማስታወሻ

(1) GRUDEM (ም. 19) ሰፋ ያለ ትምህርት ስለ መላእክት ይሰጣል።

(2) BERKHOF ገጽ 143፤ NIDCC SWEDENBORG, EMANUEL (1688-1772) ።

(3) «ክብረ ቅዱሳን» ከአባ ገብርኤል የተጻፈ ገጽ 66-68።